AgroBIG

የኢትዮጵያ-ፊንላንድ በግብርና ተኮር የንግድ ልማትን መሠረት ያደረገ የኢኮኖሚ እድገት ፕሮገራም በአማራ ክልል

# የፈጠራ፤ሠርቶ ማሳያና የምርምር ድጋፍ ፈንድ ማኑዋል



ጥር 2006

ባሕርዳር

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| 1. መግቢያ | 3 |
| 1.1 አገሮ ቢግ ፕሮገራም | 3 |
| 1.2 የማኑዋሉ አገልገሎት | 5 |
| 1.3 የማኑዋሉ ወሰን | 5 |
| 2. የፈጠራ፤ ሰርቶ ማሳያና የምርምር ድጋፍ  ፈንድ | 5 |
| 2.1 ዓላማ፤አገልግሎትና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተግባራት | 5 |
| 2.2 የፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያና ምርምር  ድጋፍ ፈንድ  የአፈጻጸም ዘዴ ማጠቃለያ | 8 |
| 2.3  የፕሮጀክት አሰተዳደር | 9 |
| 2.3.1 በክልል ደረጃ | 9 |
| 2.3.2. በወረዳ ደረጃ | 10 |
| 2.4 የትግበራ ስልት | 11 |
| 2.4.1  በወረዳ ደረጃ የፈጠራ፤ ስርቶ ማሳያና ምርምር ፈንድ ለመጠቀም | 12 |
| 2.4.2 የዚህ ፈንድ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ፕሮጀክቶች | 12 |
| 3. የፈጠራ፤ ሠርቶ ማሰያና ምርምር ድጋፍ ፕሮጀክት | 13 |
| 3.1 የዚህ ፈንድ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ አመልካቾች | 13 |
| 3.2 የድጋፍ ፈንድ ጣሪያና የአመልካቹ የመቀናጀ /መዋጮ ድርሻ | 13 |
| 3.3 የክፍያ አፈጻጸም  በፈንዱ ሴክረታሪያት አማካኝነት የሚፈፀም ሆኖ | 14 |
| 3.4. የፕሮጀክቱ ቆይታ | 14 |
| 3.5. በድጋፍ፤ ሰርቶማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ  ሊሸፈኑ የሚችሉና የማይችሉ ወጪዎች | 14 |
| 3.6 ፈረጅብዙ ጉዳች፤ ሥርዓተ ፆታና አካባቢ ጥበቃ | 15 |
| 4. የፕሮጀክት ሃሳብ አቀራረብ ሂደት | 16 |
| 4.1 የፕሮጀክት ንድፈ-ሃሳባ አቀራረብ  ግንዛቤ መፍጠርና እንዲቀርብ ጥሪ ማስተላለፍ | 17 |
| 4.2 የቀረበን የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳብ መመርመርና ማጽደቅ | 18 |
| 4.3 የፕሮጀክት ሃሰብ አዘገጃጀት | 19 |
| 4.4 ማጽደቅና አመልካቹ ውል እንዲወስድ ማሰወቅ | 20 |

| | |
|---|---|
| 5. ፕሮጀክት ትግበራ | 23 |
| 5.1 ሕጋዊ የውል ስምምነት | 23 |
| 5.2 የባንክ ሂሳብ ቁጥርና የክፍያ አፈፃፀም | 23 |
| 5.3 ግዢ | 24 |
| 5.4 የፋይናንስ አስተዳድርና የሂሳብ አያያዝ | 24 |
| 5.5 የሩብ ዓመት ክንውን ሪፖርት | 25 |
| 5.6 የፋይናንስ ሪፖርት | 25 |
| 5.7 ክትትልና ቁጥጥር | 25 |
| 5.8 የማጠናቀቂያ ሪፖርትና ፕሮጅክትን መዝጋት | 27 |
| 6. የማጠናቀቂያ ሂሳብ ምርመራ (ኦዲት) | 28 |
| 7. የፕሮጀክት ውጤትን መመዘንና የመጣውን ተፅዕኖ መዳሰስ | 28 |
| አባሪ 1፡ የፕሮጀክት ንድፈ-ሃሰብ ማቅረቢያ ቅፅ | 32 |
| አባሪ 2፡ የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳብ መገምገሚያ ቅጽ | 34 |
| አባሪ 3፡ የፕሮጀክት ሃሳብ ማቅረቢያ ቅጽ | 36 |
| አባሪ 4፡ ፈርጀ-ብዙ ጉዳዮች መከታተያ ሠንጠረዥ | 38 |
| አባሪ 5፡ የፕሮጀክት ሃሳብ መገምገሚያ ቅፅ | 39 |
| አባሪ 6 ሕጋዊ የበጀት ድጋፍ የውል ስምምነት | 41 |
| አባሪ 7፡ የሩብ ዓመት የአፈፃፀም ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ | 44 |
| አባሪ 8፡ የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ | 46 |
| አባሪ 9፡ የበጀት ድጋፍ መጠየቂያ ቅፅ | 47 |
| አባሪ 10፡ የፕሮጅክት ማጠናቀሪያ ሪፖርት ቅፅ | 48 |
| አባሪ 11፡ የቡድን ተኮር ማወያያ ቅፅ | 49 |
| አባሪ 12፡ የተጠቃሚዎችን መስክርነት ማሰባሰብ ቅፅ | 50 |

# 1. መግቢያ

## 1.1 የአግሮ ቢግ ፕሮገራም

አግሮቢግ በኢትዮጵያና በፊንላንድ መንግስታት መካከል በተደረገ ስምምነት የግብርናን ምርት ከንግድ ጋር በማተሳሰርና ለማበልጸግ በክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አሰተባባሪነት የሚተገበር ፕሮገራም ነው፡፡
ዋነኛው የፕሮገራሙ ዓላማ የግብርናን ምርት በማሰደግ ድህነትን ለመቀነስ በሚደረገው እርብርብ የበኩሉን አስተዋጽ ለማበርከት ነው፡፡

የፕሮገራሙ ግንባር ቀደም ተጠቃሚዎች 1) ፕሮገራሙን ለመተግበር በተመረጡ ወረዳዎች የሚገኙ ድሃ የአርሶ አደር ማህበረሰቦችና አባ/እማወራዎች በተለይ ለድህነት የተጋለጡ የማህበረሰብ ክፈሎች፤ 2) በግብርና ሥራ የተሰማሩ ማህበራት፤ አቀነባባሪ ኩባንያዎች እና፤ 3) የመንግስትና የግል ድርጅቶች ሲሆኑ ከፕሮገራሙ የአቅም ግንባታ ተግባራት ተጠቃሚ ናቸው፡፡

አግሮቢግ የ3 ዓመት ፕሮግራም ሲሆን ቆይታው እንደ አውሮፓዊያን አቆጠጠር ከ2013-2015 ድረስ ነው፡፡ ፕሮገራሙ በመጀመሪያው ምዕራፍ በሜጫና ፎገራ ወረዳዎች በግብርና ሥራ ዘርፍ (ሽንኩርትና ድንች) ላይ የተሰማሩትንና አንስተኛ ባለይዞታዎችን የሚደግፍ ሆኖ በሁለተኛው ምዕራፍ ተጨማሪ ወረዳዎችንና ሌሎች ምርቶችን አካቶ ድጋፉን የማስፋፋት እቅድ ይዟል፡፡

አግሮቢግ ፕሮገራም ሥራዎችን በ3 ምደቦች ከፍሎ ያከናወናል፡፡
**የእሴት ሰንሰለት ልማት፡** የባለድርሻ አካላትን ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ የጋራ ግንኙነት እንዲፈጥሩ ማመቻቸት፤ ችግሮች እንዲለዩና መፍትሄያቸውን በጋራ እንዲያሰቀምጡ ማገዝ ትርፋማነት የሚገኝበትን ዘዴ ለመፈጸም የጋራ ድርጊት መርሀ ግብር መንድፍን ያጠቃልላል፡፡

**የአገልግሎት አሰጣጥን ማጎልበት፡** በእሴት ሰንሰለት ልማት ላይ ሚና የሚኖራቸውን ተዋንያን ምርታቸውን እንዲያሳድጉ ንግዳቸውን እንዲያሰፋፉ፤ የማቀነባበር አቅማቸውን እንዲያሳድጉ የገብያ ትስስራቸው እንዲጠነክር የአገልገግሎት አሰጣጣቸውን በተሻለ ደረጃ ለማሳደግ የሚደረግ ድግፍ ነው፡፡

**የፋይናንስ ተደራሽነት፡** ቁጠባንና የብድር አገለግሎትን ማበረታታት፤ የሞባይል የባንክ አገልግሎት በአርሶ አደሩ ዘንድ ለማስተዋወቅና ለመተግበር፤ በተመረጡ ምርቶች ላይ ፈጠራን አካቶና የእሴት ሰንሰለቱን የሚያለሙ ጉዳች በገንዘብ ለመደገፍ ሲሆን በዚህ ረገድ ፕሮገራሙ 3 የተለያዩ የፋይናንስ አቅረቦት ይኖረዋል፡፡ እነሱም፤-

- የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ
- የእሴት ሰንሰለት ድጋፍ ፈንድ
- የፈጠራ፤ ሰርቶ ማሳያና የምርምር ድጋፍ ፈንድ ናቸው፡፡

ይህ ማኑዋል የሚየተኩረው በሦስተኛ ደራጃ ለተጠቀሰው ለፈጠራ፤ ሰርቶ ማሳያና የምርምር ድጋፍ ፈንድ ላይ ሲሆን በተከታታይ ለመቀናጀና ለእሴት ሰንሰለት ድጋፍ ፈንድ የየራሳቸው ማኑዋል ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡

በአማራ ክልል በግብርና እሴት ሰንሰለት ላይ ድጋፍ የሚያደርጉ ሌሉች አጋር ድርጅቶች አሉ፡፡ የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል (Agricultural Growth Programme, Ethiopian Nile Irigation

& Drainage Project, The Rice Value Chain of Mennonite Economic Development Associates). እነዚህ ፕሮጀክቶች ባለፉት ጊዜያት በፈንድ አስተዳደር ያካበቱትን ልምድና ተሞኩሮ አካፈለዋል፡፡ በእነዚህ አጋር ድርጅቶች ይንቀሳቀሱበቸው የነበሩ አካባቢዎች፤ ለእሴት ሰንሰለት የተመረጡት ምርቶችና የሚሰጡት ድጋፍ ይለያያል፡፡ ይህን ማኑዋል ለማዘጋጀት ሲባል አጋር ድርጅቶች ይከተሉት የነበረውን ስልትና ይጠቀሙበት የነበረውን ማኑዋሎቻቸው ላይ እንዲሁም ወጥ የሆነ አሰራርን ለማስፈን ድግግሞሽን ለማስወገድ ጥናት ተደረጓል፡፡

### 1.2 የማኑዋሉ አገልግሎት

የዚህ ማኑዋል አገልግሎትስለ እሴት ሰንሰለት ፈንድ ትግበራ በሁሉም ባለድርሻ አካላት ዘንድ ግለፀኝነትንና ተጠያቂነት በውል እንዲረዱት ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህ ማኑዋል ፕሮጅክቱ ተጋባራዊ በሚሆኑባቸው ወረዳዎች ውሰጥ ስለፈንዱ ዓላማና መርሆች፡ ተቋማዊ አደረጃጀት፡ በፈንዱ የሚሸፈኑና የፈንዱ ተጠቃሚ ለመሆን ለማመልከት የሚከተሉዋቸውን ሂደቶችንና ይሁንታን ለማግኘት የሚከናወኑ ተግባራትን እንዲሁም የክትትልና ምዘና ሄደት አካቶ የያዘ ነው፡፡

ማኑዋሉ ሁሉንም አካላት (ተጠቃሚ ለመሆን የሚያመለክቱትን፤ ፈፃሚ አካላትና የፈንዱን አሰተዳዳሪዎች) በፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት ስለሚኖራቸው ሚናና መከትል ስለሚገባቸው ሂደቶች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያግዛቸዋል፡፡

### 1.3 የማኑዋሉ ወሰን

ይህ ማኑዋል በመጀመሪያው አንድ ዓመት ፕሮጅክቱ የሙከራ ዘመን እንዲያገለግል ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ የሙከራ ጊዜም በሚገኘው ተሞክሮ የፈንዱ አስተባባሪ ጽ/ቤት እንዳስፈላጊነቱ ክለሳ በማደረግ በፕሮገራሙ ሥራ አመራር ቦርድ እንዲጸድቅ ይደርጋል፡፡

## 2. የፈጠራ፤ ሰርቶ ማሳያና የምርምር ድጋፍ ፈንድ

### 2.1 ዓላማ፤አገልግሎትና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተግባራት

የተሻሻለና ፈጠራና መሰረት ያደረገ የግብርና ሥርዓት ሲባል በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶች፤ እንተርፕራይዞችና ግለሰቦች መካከል ያለ ትስስርና የእነዚህ አካለት የጋራ ጥረት በማድረግ አዳዲስ ሂደቶችችን በመከተል አዲስ ምርት ለማገኘት የሚደረግ እንቅሰቃሴ ነው፡፡

**የዚህ ፈንድ ጥቅል ዓላማዎች፡**

- በተመረጡ ምርቶች ላይ የተሻሻለ እሴት ለመጨመርና የተሻለ ገበያ እድል እንዲያገኙ ለማድረግ በዘርፉ የተሰማሩትን ባለድረሻ አካላት አቅማቸውን ለመገንባት
- ተመራማሪዎችን፤ የግሉን ሴክተር አምራቾችንና ሌሎች ተዋንያንን ትስስር እንዲፈጥሩ በማድረግ በተመረጡ ምርቶች ላይ የተሻለና አዲስ ፈጠራ ይዘው እንዲመጡ ለማበረታታት

- የግብርናውን ዘርፍ እንዲያድግ እገዛ በማድረግ በድህነት ቅነሳ ላይ የበኩሉን አስተዋፅዖ ለማበርከት በወነኛነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

**የዚህ ፋይናንስ ምንጭ ዝርዝር አገልግቱ <u>የመፈጸም አቅምን ከማስደግ</u> ጋር የተሳሰረ ነው፡፡**

- በምርቶች ላይ ተሳታፊ የሆኑትን ባለድርሻ አካላት በማገናኘት ቅደሚያ የሚሰጣቸውን ተገባራት እንዲያስቀምጡ ለማደረግ፤ የአፈጻጸም እጥረቶቻቸውን እንዲለዩ፤ አጥረቶችን ለማሰወገድ ምን እርምጃ መውሰድ እንደለባቸው፤ ምን ውጤት እንደሚጠበቁ እንዲወያዩ ለማድረግና በአጠቃላይ የእሴት ሰንሰለትን ለማልማት የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ ነው፡፡
- የግሉንና የመንግስትን አገልገሎት ሰጪ ዘርፎች አዲስ ቴክኖሎጂዎችን እንዲለዩ እንዲቀረፁ፤ አዲስ ሃሳብ እዲያፈልቁ፤ አዲስ የማምረትና የማቀነባበር ዘዴ የማሰየት፤ ብቃታቸውን ለማሳደግ፤ እነዚህ ፕሮገራሞች እንዴት እንደሚቀረፁና ለዚህ ተገባር የተመደበውን ገንዘብ ለመጠቀም አንዴት እንደሚያመለክቱ ይማሩበታል፤
- አርሶ ደሮችና አደረጃጀታቸው ከባቢያዊ እውቀታቸውን በመጠቀም አዲስ ፕሮጀክቶችንና ስልቶችን በማፈለቅ ከዚህ በፊት የፋይንንስ ምንጭ አግኝተው የማያዉቁትን በዚህ ፈንድ የመጠቀም ዕድል ለመስጠት
- በተመራማሪዎችና በስርፀት (በኤክስቴሽን) በለሙያዎች የተለዩ ቴክኖሎጆዎችን በማሳ ላይ የሚደረጉ ሰርቶ ማሳያዎችን ለመደገፍ፤ የሚገኘውን አውቀትና ልምድ ወደ ማህበረሰቡ እንዲፀረስ እገዛ ለማድረግ
- በግብርና ምርት አቀነባባሪዎችና በአንሰተኛ ባለይዞታዎች መካካል ትስስር እንዲፈጥሩ በማደረግ በመካከላቸው አንዱ በሌላው አምነት እንዲኖረው ለማደረግ፤ ከግብይት ጋር የተያያዙ የተሻሉና ጥሩ ተሞክሮዎችን አንዲለዋወጡ ለማሰቻል፤
- ሙያዊ ምክር ለመስጠት ለምሳሌ አዲስ ምርት ሰለማምረት፤ የእርሻ አስተዳደር ምርጥ ተሞክሮዎችን ለማካፈል፤ አደጋ ትንተናና ቁጥጥር (Hazard Analysis Critical Control Point)፤ ከግብይት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ፤ ለምርቱ ስያሜ ስለሚሰጥበት፤ ስለስርጭት … ወዘተ
- አግልገሎት ሰጪዎችን ከፋይናንስ አቅራቢዎች ጋር ለማገናኘት ለምሰሌ፤ መረጃ በመስጠት፤ እንዴት ማመልከት እንደሚቻል ስልጠና በመስጠት፤ በፈጠራ ፤በሰርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድን የመጠቀም እድል በመስጠት ሊሆን ይችላል፡፡

**የፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያና ምርምር የድጋፍ ፈንድ የሚጠበቅ ውጤት ስዕላዊ መገለጫ**



የፈጠራ፤ ሰርቶ ማሳያና የምርምር ድጋፍ  ፈንድ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተግባራት ለእሴት ሰንሰለት  በተመረጡ አካባቢዎችና ምርቶች ጋር  የተያያዘ ሲሆን የሚከተሉትንያካትታል፡፡

- በተመረጡ ምርቶች እሴት ሰንሰለት ላይ በተለይ በሜጫና ፎገራ ወረዳዎች የፈጠራ፤ ሰርቶ ማሳያና የምርምር ላይ ድጋፍ ማደረግ ፤ ውጤቱም፤ ገበሬዎችን፤ ነጋዴዎችን  የግብርና ምርት ውጤቶችን የሚያቀነባበብሩትን ሸማቾችን የሚጠቅምና የሚያበረታታ መሆን አለበት

- የድጋፍ ፈንዱ ለመንግስት ተቋማትና ለግሉ ዘርፍ አመልካቾች የተዘጋጀ ሲሆን የሚቀርቡ የፕሮጀክት ሃሳቦች በወረዳው በተመረጡ ምርቶች ላይ በተዘጋጀው የድርጊት መርሃ-ግብር  የተካተተና የተለዩ እጥረቶች በመፍታት ላይ ያተኮረ መሆን አለበት

- አግሮቢግ በመጀመሪያው ምዕራፍ  ሽንኩርትና ድንችን መርጦ በፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ፈንድ ድጋፍ  ለማድረግና በቀጣይ ሌሎች ምርቶችን ለማካተት ታስቧል፡፡

- በከፍተኛ ደረጃ የገቢ ምንጭ ማስገኛ ሊሆኑ የሚችሉ፤ ዘመናዊና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ በግብርና የተሰማሩትን በሙከራ ደረጃ ድጋፍ ማድረግ (ለምሳሌ ወደውጭ በሚላኩ ምርቶች በማምረት ላይ የተሰማሩትን)

- ሴቶችና በኢኮኖሚ ረግድ ተጠቃሚ ያልነበሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በዚህ ፈንድ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ

## 2.2 የፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ የአፈጻጸም ዘዴ ማጠቃለያ

ከዚህ በታች የተመለከተው ሠንጠረዥ ስለ ፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ አጠቃላይ ገፅታን ያስረዳል፡፡ ዝርዝር መረጃ ምዕራፍ 3 ተካቷል፡፡

| | ፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ |
|---|---|
| አገልገሎት | አርሶአደሮችን፤ አቀነባባሪዎችን በንግድ የተሰማሩትንና አገልግሎት ሰጪዎችን የእሴት ሰንሰለትን ሊያሳድግ በሚችል የፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያን ምርምር ስራዎችን በመለየት፤ በመቅረጽና የድርጊት መርሃግብር ዝግጅትና ድጋፍ ለማድረግ፤ የአዋጪነት ጥናት ለማከናወን፤ አጋር ድርጅቶችን ለመለየት፤ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመለየትና የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ሊያካትት ይችላል፡፡ |
| ዓይነት | የመቀናጀ ፈንድና ድጋፍ |
| ሊሰጥ የሚችል ከፍተኛው የፋይናንስ ድጋፍ መጠን | ለአንድ የፕሮጀክት 52,000 ዩሮ (የኢትዮጵያ 1,300,000 ብር) |
| የክፍያ አፈፃጸም | የተከናወነው ተግባር አፈፃፀም እየተለካና<br>የማጠናቀቂያ ሪፖርት ሲቀርብ |
| የፕሮጀከቱ ቆይታ | እንደፕሮጀክቱ ባሀሪ የሚወሰን በአበዛኛው 1 ዓመት |
| ወለድ | አይኖረውም |
| ዋስትና | አያስፈልግም |
| የፋይናንስ ድጋፉን የሚያስተዳድረው | ገ/ኢ/ል/ቢሮ (አግሮቢግ) |
| የራስ መዋጮ (መቀናጀ በጀት) ድርሻ | ጠያቂው የአጠቃላይ ወጪዉን 15% በራሱ መሸፈን ይጠበቅበታል |
| የተጠቃሚዎች ቅድመ ሁኔታዎች | ፕሮግራሙ በሚተገበርበት ወረዳ በ100 ኪሎ ሜትር ርቀት ባልበለጠ የሚኖርና ከእሴት ሰንሰለት ምርት ጋር ቀጥተኛ በሆነ ዘርፍ የተሰማራ |
| በመሠረታዊነት መዋለ ነዋይን ኢንቨስት ለማደርገ የሚጠበቁ ቅድመ ሁኔታዎች | 1. የስራ እቅድ (የአቅም ግንባታ ሃሳባ)<br>2. የቴክኖሎጂ ፈጠራ ወይም ሰርቶ ማሳያ |

| | |
|---|---|
| | እቅድ<br>3. የእሴት ስንሰለትን የሚያጠናክር የምርምር ወይም የጥናት መርሃ-ግብር<br>4. የቡድና አባላትን በእሴት ሰንሰለቱ ተጠቃሚ ለማድረግ ያለው ዕድል<br>5. አዲስ ቴክኖሎጂን ወይም ጥሩ ተሞክሮን ለመለየት፤ ለመሞከርና ለማስተዋወቅ |
| **ልዩ ቅድመ ሁኔታ** | ለሁሉም ክፍት ነው። (ለአርሶአደሮች አደረጃጀት፤ ማህበራት፤ ካምፓኒዎች፤ የምርምር ተቋማትና ሌሎች፤ ሆኖም ግን ግለሰብን አይመለከትም። |

## 2.3 የፕሮጀክት አሰተዳደር

በሀገር አቀፍ ደረጃ የኢፌዲሪ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒሰቴርና የፊንላንድ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር በመንግሰታት መካከል የተፈራረሙ ሲሆን በአጠቃለይ በፕሮገራሙ ላይ ስልጣን አላቸው።

### 2.3.1 በክልል ደረጃ

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሰት ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በክልል ደረጃ የአግሮቢግ ፕሮገራም የተፈራረመ ሲሆን በክልል ደረጃ የመምራት ሃላፊነት አለው።

**የአግሮ ቢግ የሡራ አመራር ቦርድ**

የሥራ አመራር ቦርዱ ፕሮገራሙን በተመለከተ ስትራቴጂካዊ የመጨረሻ ውሳኔዎችን የመወሰን፤ ከፍተኛው ውሳኔ የሚሰጥ አካል ነው። ቦርዱ በአመት ከ1-2 ጊዜ ይሰበሰባል። የቦርዱ አባለትም ገ/ኢ/ል/ሚ/ር፤ከገ/ኢ/ል/ሚ/ ቢሮ፤ ከግብርና ቢሮ፤ ከንግድና ትራንስፖርት ቢሮ፤ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ፤ አ/ብ/ቁ/ተ/፤ የግል ተቋማት ተወካይ እና ከፊንላንድ መንግስት ውጭ ጉዳይ ሚ/ር (ኢምባሲ) በተወከሉ ከፍተኛ ባለስልጣናት የሚመራ ነው።

**የአግሮቢግ ክልላዊ የቴክኒክ ኮሚቴ**

ኮሚቴው በየወሩ የሚሰበሰብ ሲሆን ፕሮገራሙ በአገባቡ መተግበሩን፤ ውጤት መገኘቱንና የፕሮገራሙ ገንዘብ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ መዋሉን ያረጋግጣል። ለፕሮገራሙም የሙያ ድጋፍ ይሰጣል።

**የፈንድ ሴክሪታሪያት**

የፈጠራ፣ ሠርቶ ማሳያን ምርምር ፈንድን በክልል ደረጃ የማስተዳደሩ ሃላፊነት የክልሉ ገ/ኢ/ል/ቢሮ ሲሆን ቢሮው የፈንዱን የዕለተ ከዕለት ተገባር ለማከናወን ለአግሮ ቢግ ፕሮገራም ድጋፍ ዩኒት ውክልና ይሰጣል፡፡ ዩኒቱም የፕሮገራሙ ጸሃፊ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን በገ/ኢ/ል/ ቢሮ በሚሰየም የፕሮገራም ዳይሬክተርና የቴክኒክ አማካሪ ቡድን በሚመራ የውጭ አለምአቀፍ ቡድን መሪ ይመራል፡፡

የፈጠራ፣ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ፈንድን በተመለከተ ማንኛውም ጉዳይ ለፈንዱ ሴክሪታሪያት መላክ የሚቻል ሲሆን ጉዳዩ ለሚመለከተው የክልል ወይም ወረዳ ኮሚቴ እንዲመለከተው ሊመራው ይችላል፡፡

## 2.3.2. በወረዳ ደረጃ

የአግሮቢግ ፕሮገራም በሚተገበርባቸው ወረዳዎች የተለያዩ ኮሚቴዎች ይዋቀራሉ፡፡

**የወረዳ ስቲሪንግ ኮሚቴ**

ስቲሪንግ ኮሚቴው በወረዳ አስተዳዳሪ የሚመራ ሆኖ በየሩብ ዓመቱ የሚሰበሰብ ሲሆን በመሃል አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም እንደሁኔታው ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡ የኮሚቴው አባላትም የገ/ፐ/ጽ/ቤት ሃላፊ፣ የግብርና ጽ/ቤት ሃላፊ፣ የንግድና ትራንስፖርት ጽ/ቤት ሃላፊ፣ የገበሬዎች ማህበራት ዩኒዬን ሃላፊ፣ በአካባቢው የሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያድ) እና ሁለት የግል ዘርፍ ተወካዮች ይሆናሉ፡፡

ኮሚቴው የፕሮግራሙን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ፣ በጀትና የክንውን ሪፖርት ያጸድቃል ይመረምራል፣ ፈርጀ ብዙ ሲክተሮችን ያስተባብራል፡፡ በወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ ታይቶ የሚመጣለትን የፕሮጀክት ሃሳብ ተቀበሎ የጸድቃል፡፡ ይህን የፋይናንስ ምንጭ ለመጠቀም የሚቀርቡ የፕሮጀክት ሃሳቦች ጥሪ በምን መልኩ መተላለፍ እንዳለበት ይወስናል፡፡ በክልል ደረጃ ውሳኔ የሚሹትን ጉዳዮች አይቶ ያስተላለፋል፡፡

**የወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ**

ይህ ኮሚቴ ለወረዳው ስትሪንግ ኮሚቴ ሙያዊ ምክር የሚሰጥ ሲሆን በየወሩ እተሰበሰበ የሚቀርቡትን የፕሮጀክት ሃሳቦችን እየገመገመና የውሳኔ ሃሰብ አካቶ ለወረዳው ስቲሪንግ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡ ኮሚቴው በገ/ፐ/ጽ/ቤት ሃላፊ ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ አባላቱም የገ/ፐ/ጽ/ቤት ሙያተኛ፣ የግብርና ጽ/ቤት ተወካይ፣ የንግድና ትራንስፖርት ጽ/ቤት ተወካይ፣ የገበሬዎች ማህበራት ዩኒዬን ተወካይ፣ በአካባቢው የሚገኙ መያድ ተወካይ፣ የግል ዝርፍ ተወካዮች፣ የአግሮ ቢግ የወረዳ አስተባበሪና የገ/ፐ/ጽ/ቤት የፋየናንስ ኦፊሰር በኮሚቴው ይሳተፋሉ፡፡ እንደአስፈላጊነቱ የዞን ገ/ኢ/ል/ በኮሚቴው ሊገኝ ይችላል፡፡

**የወረዳ እሴት ሰንሰለት ፈንድ ባለድርሻ አካላት**

በእያንዳንዱ ምርት የተቋቋመው የወረዳ የፈጠራ፣ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ ባለድርሻ አካላት በየሩብ ዓመቱ የሚሰበሰብ ሲሆን የግብርና ጽ/ቤት ሰበሳቢነትና በአግሮቢግ ወረዳ አስተባበሪ በመታገዝ የመራል፡፡ ተሰብሳቢዎች በሚገናኙበት ጊዜ በዋጋ ሰንሰለት ማበልጸግ ባሉ ችግሮችና

እጥረቶችን ለመቅረፍ በሚወሰዱ የመፍትሄ ሃሳቦች ላይ ይወያያል፤ ሊያከናውኑ ያሰቡትንም የድርጊት መርሃ-ግብር ያዘጋጃሉ፡፡

### የወረዳ ፈንድ ሴክረታሪ

የአግሮቢግ ወረዳ አስተባባሪ የፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያን ምርምር ድጋፍ ፈንድ የፕሮጀክት ሃሳብ ሊያቀርቡ የሚችሉትን አካላት ለመጋበዝ የሚደረግ ጥሪን የስተባብራል ያመቻቻል፡፡ አስተባባሪው የፕሮጀክት ሃሳብ የሚየቀርቡትን አመልካቾች ከወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴ ጋር በመሆን እንዴት የፕሮጀክት ሃሳብ መጻፍ እዳለበት እገዛ ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የወረዳው አግሮቢግ አስተባባሪ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

- ከወረዳ ባለድርሻ አካላት በመሆን የፕሮጀክት ሃሳብ አቀራረብና የአፈቃቀድ ሂደት ያስረዳል ያሳያል፤
- የተዘጋጀውን የድጋፍ ፈንድ በማስተዋወቅ ረገድ የወረዳውን ኮሚቴ ያግዛል ለምሳሌ ሥለ ፐሮጅክት ሃሳብ አቀራረብ ለሚመለከታቸው አካላት ግንዛቤ መፈጠር
- የፕሮጅከት ሃሳበ ያቀረቡ አካላትና የፕሮጅከት ሃሳቦችን መረጃ ይይዛል
- ሊቀርቡ የሚችሉ የፕሮጀክት ሃሰቦችን ያሰረዳል የመስክ ጉብኝት የመቻቻል
- ለአመልካቾች የኮሚቴውን ውሳኔ ያሳውቃል፤ ስእሴት ሰንሰለት ድጋፍ ፈንድ የሚያስፈልጉ ቅደመ ሁኔታዎችና ስለዋናው የፕሮጀክት ሃሳብ አቀራረብ ስለጠና ይሰጣል
- የቀረቡ የፕሮጀክት ሃሳቦች በሙያተኛ እንዲገመገሙ ያደረጋል
- ተቀባይነት ያገኙ የፕሮጀክት ሃሰቦችን የሚያውቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል
- ከተመረጡ አመልካቾች ጋር ውል እንዲፈረም ያስተባብራል፤ በውሉ መሰረት ክፍያ መፈፀሙን ይከታላል፤
- የፕሮጀክት ክትትልና ምዘና እንዲካሄድ ያደርጋል

## 2.4 የትግበራ ስልት

የወረዳ የእሴት ሰንሰለት ባለድርሻ አካላት በተመረጡ ምርቶች ላይ ያልን ችግር የመለየትና ችግሮችን ለመፈታት የድርጊት መርሃ-ግብር መንደፍ የመሪ ሚና ይኖረዋል፡፡ የፈጠራ፤ ሠርቶ ማሰያና ምርምር የድጋፍ ፈንድ ስራ ላይ የሚውለው በህዝብ ተቋማትና በግሉ ዘርፍ አማካኝነት ሲሆን አስቀድመው በተለዩ የዋጋ ሰንሰለት ችገሮች ዙሪያ ይሆናል፡፡

### 2.4.1 በወረዳ ደረጃ የፈጠራ፤ ስርቶ ማሳያና ምርምር ፈንድ ለመጠቀም

በወረዳ ደረጃ ከሚገኙ በለድርሻ አካላት ጋር የመጀመሪያው ስበሰባ በአግሮቢግ አመቻችነት ይካሄዳል፡፡ ስበሰባው የእሴት ሰንሰለት ችግሮች ላይ በመወያየት፤ የግንዘቤ ክፍተቶችንም ይዳስሳል፡፡ የአግሮቢግን ፋይናንስ በመጠቀም የአርሶአደር አደረጃጀቶች፤ መሠረታዊ ማህበራትና የተለያዩ የአደረጃጀት ትስስሮች በጋራ ምርታማነት የሚያሳድጉበትን ዘዴ የሚለዩበት ይሆናል፡፡ በውይይት የተለዩ ጉዳዮች ከዚህ በፊት የተጠኑ ጥናቶች ለወረዳ ባለድረሻ አካላት ለድረጊት መርሃ-ግብር ዝግጅት መነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ይህ ሂደት ለፈጠራ፤ ስርቶ ማሳያና ምርምር ለሚተገበሩ ስራዎች መሰረት ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው፡፡ **ለምሳሌ**

- በእሴት ሰንሰለት ላይ ለሚደረግ ምርምር ለመደገፈ፤ የግንዛቤ ፈጠራ ለማካሄድ፤ እንደአስፈላጊነቱ የስልጠና ዝግጅት ለማድረግ
- በቴክኖሎጂ በኩል የታዩትን ክፍተቶች ለመለየትና ለመደገፍ
- የእሴት ሰንሰለት ተዋንያንን የፕሮጀክት ሃሰብ ጥያቄ አቀራረብን የድርጊት መርሃ-ግብር አዘገጃጀት ድጋፍ ማደረግ፤ ይህም የተሻሻለ ዘር መጠቀም፤ አውቅና ያገኘ ዝርያ ማቅረብ፡ የማምረቻን የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂ አጠቃቀም፤ የማቀነባበር ቴክኖሎጂ ሁሉ ያጠቃልላል
- ጠቃሚና አስፈላጊ የሆኑ ጥናቶችን ከባለድርሻ አካላት ጋር መለየት፤
- የግብርና ነክ አቀነባበሪያዎችን፤ አነስተኛ ባለይዞታዎች አቅም ለማሳደግ፤ አዲስ ቴክኖሎጂን ከመተግበር ጋር ተያይዞ የሚመጣን ስጋት ለመቀነስ፤ የተለያዩ አካላትን አጋርነት ማጠናከር፤ አዳዲስ ግብይቶችን ለማስፋፋትና በተዋንየኑ መካክል የእርስ በርስ እምነት እንዲፈጠር ማድረግ
- የእሴት ሰንሰለት ተዋንያንን ከፋይናንስ ተቋማት ጋር ለማተሳሰር /ለማገናኘት

በወረዳው የእሴት ሰንሰለት ድርጊት መርሃ-ግብር ጋር እሰከተጣጣመ ድረስ ማንኛውም የግልና የመንግስት ተቋም የፈጠራ፤ ሠርቶማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድን ለመጠቀም ለሁሉም ክፍት ነው፡፡ የወረዳው ባለድርሻ አካላት የግሉ ዘርፍና የመንግስት ተቋም (ግብርና፤ ግብርና ምርምር፤ ዩኒቨርሲቲዎች...ወዘተ) በእሴት ሰንሰለት ዙሪያ ባሉት ውስንነቶች እንዲሳተፉ የማነቃነቅ ሃላፊነተ አለበት፡፡ በተጨማሪም የአርሶ አደር አደረጃጀቶች፤ ማህበራት፤ የንግድ ድርጅቶች፤ የምርምር ተቋማትም በዚህ የፋይናንስ ምንጭ እንዲሳተፉ መጠየቅ ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.4.2 የዚህ ፈንድ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ፕሮጀክቶች

- ስለጠና፤ አቅም ግንባታ፤ የገበያ ጥናት፤ የስራ እቅድ ፤ የማግባብያ ውይይቶች ለማካሄድ
- በምርምር የተገኘን ምርት ማለመድ፤ ምርምር ለማካሄድ፤ ምርትን ለማስተዋወቅ፤ የረጅም ጊዜ የአቅም ግንባታ (ሙያተኛ መመደብ)፤ ምርትን ለማሻሻል፤ምርትን ወደወጭ ለመላክ፤ የገበያ መረጃ ለማገኘት
- የግልና የመንግስት አገልገሎት ሰጪ አካላትን ትስስር ለማጠናከር

- ገበሬዎችን በተመሳሳይ ተግባር ከተሰማሩ ድርጅቶችና ቁልፍ ተዋንያን ጋር ለማገናኘት (ለምሳሌ በማምረት ላይ የተሰማሩትንና ምርታቸውን የሚረከቡትን አካላት ትስስር ማጠናከር)
- ለክህሎት ወይም እውቀት ለማሸጋገር፤ችግር ፈቺ ምርምር ለማድረግ፤ ተያያዥ የሆኑ ስለጠናዎች ለመስጠት
- ገበያና የውጭ ንግድን ለማስፋፋት፤ የገበያ ጥናት/ምርምር፤ የጥራት ፍተሻና የብቃት መረጋገጫ ለተያያዙ ተግባራት፤
- የገበያ መረጃ ሥርዓት፤ ከማምረት ጋር ለተያያዙ ተግባራት፤ የጥራት ደረጃና ቁጥጥር፤ ምርታማነትን ለማሰደግ ለሚደረግ ጥናት

## 3. የፈጠራ፤ ሠርቶ ማሰያና ምርምር ድጋፍ ፕሮጀክት

### 3.1 የዚህ ፈንድ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ አመልካቾች

ሀ. የእሴት ሰንሰለት ተዋንያን (ገበሬዎች፤ የተለያዩ የአርሶ አደር አደረጃጀቶች፤ የሸማች ማኅበራት፤ በግብርና ድለላ፤ በንግድ፤ ማቀነባበርና ወጭ ንግድ የተሰማሩ)

ለ. የፋይናንስና የሥራ አፍላቂ አግልግሎት ሰጪዎች

ሐ. የአቅም ግንባታ አገልግሎት ሰጪዎችና የምርምር ተቋማት ወዘተ... ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡

በዚህ የፋይናንስ ምንጭ ተጠቃሚ ከሚሆኑት ብቁ ተሳታፊዎች መካከል ከግል ተቋማት የሙያ ወይም የጾታ ማህበር፤ የአገልግሎት ስራ ማህበራት፤ ካምፓኒዎች፤ የንግድ ማህበር፤ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች...ወዘተ ሲሆኑ ከመንግሰት ዩኒቨርሲቲዎች፤ የምርምር ተቋማት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ለፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ከተያዘው በጀት ላይ ቢያንስ የድጋፍ ፈንዱን 50% የግሉ ዘርፍ ተጠቀሚ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ይሁን እንጂ የፋይናንስ ድጋፍ አሳማኝ የፕሮጀክት ሃሰብ ይዞ ለቀረበ ብቻ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

በአግሮቢግ ፕሮግራም ድጋፍ ተቀጥሮ የሚሰሩ ሰዎች ወይም ሙያተኞች የዚህ ፈንድ ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም፡፤ የአመልካቹ ድርጅት ተወካይ የሆነ ሆኖም አግሮቢግ ፕሮገራም ባዋቀረው ኮሚቴ ውሰጥ አባል ሆኖ የሚቀርቡ የፕሮጀክት ሃሳቦችን የሚገምግም ሙያተኛ ወይም ግለሰብ ለዚህ ድጋፍ ፍንድ በቁ አያደርገውም፡፡

### 3.2 የድጋፍ ፈንድ ጣሪያና የአመልካቹ የመቀናጆ /መዋጮ ድርሻ

ለአንድ ፕሮጀክት ከፕሮግራሙ ድጋፍ የሚደረግ የገንዘብ መጠን ከፍተኛው 52,000 ዩሮ (የኢትዮጵያ 1,300,000 ብር) ሲሆን ዝቅተኛ የገንዝብ መጠን ገደብ አይኖረውም፡፡

የፕሮጀክት ሃሳበ ጥያቄዎች ከየትኛውም አቅጣጫ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ የአርሶ አድሮች አደረጃጀት የአከባቢን እውቀት መሰረት አድርጎ መጠናኛ ወጪ ከሚጠይቅ አንስቶ በአነጻሩ ደግሞ የምርምር ተቋማትና የግል እንተርፕራይዞች መጠነ ሰፊ ሥራዎችንና ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ፕሮጀክት ሃሳቦች ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ሁሉም የፕሮጀክት ሃሰቦች ለወረዳው ስቲሪንግ ኮሚቴ ቀርቦ በማወዳደሪያ መስፈርቶች ተለይተው በሚወጣው ወጪ ተመጣጣኝ ወይም የተሸለ ጥቅም ለሚያስገኙት ውል እንዲወስዱ ይደረጋል፡፡

**የአመልካቹ የመቀናጀ በጀት ድርሻ**

ከዚህ ፕሮጀክት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያመለክቱ አካላት በቅደሚያ የፕሮጀክቱን 15% በጥሬ ገንዘብ በዚሁ ተግባር በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ዝቅተኛ የሆነ የአመልከቹ የመቀናጀ መዋጮ የተደረገበት ምክንያት በገንዘብ እጥረት ተሳታፊዎችን እንዳይገድብ ታስቦ ነው፡፡ የመንግስት ተቋማት የሚፈለግባቸውን ድርሻ በዓይነት ሊያዋጡ ይችላሉ፡፡

### 3.3 የክፍያ አፈጻጸም በፈንዱ ሴክረታሪያት አማካኝነት የሚፈፀም ሆኖ

ከፕሮጀክት ሃሳቡ ጋር የጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ሰንጠረዥ ተያይዞ መቅረብ ያለበት ሲሆን ይህ ገንዘብን ለመልቀቅ ከሚያስፈልጉት ነገሮች አንዱ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሦስት መንገዶች ክፍያው ሊፈፀም ይችላል፡፡ እነሱም፡-

ሀ) ቅደሚያ ክፍያ
ለ) ክንውኑ እየተገመገመ ወይም
ሐ) የፕሮጀክቱ የማጠናቀቂያ ሪፖርት ሲቀረብ ይሆናል፡፡

### 3.4. የፕሮጀክቱ ቆይታ

የፕሮጀክቱ ቆይታ እንደ በትሮጅክቱ ባህሪ ዓይነት በተናጠል እየታየ የሚወሰን ቢሆንም በመጀመሪያው ምእራፍ ግን ከ1 ዓመት ባይበልጥ ይመረጣል፡፡

### 3.5. በድጋፍ፣ ሰርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ ሊሸፈኑ የሚችሉና የማይችሉ ወጪዎች

ለዚህ ድጋፍ ፈንድ ብቁ የሆኑ ወጪዎች ብቻ በፕሮጀክቱ ገንዘብ ይሸፈናሉ፡፡ እነዚህ ወጪዎች የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

- **የሠራተኛ ደመወዝና የቴክኒክ ወጪዎች፡** የሠራተኛ ደመወዝ፣ ምንዳ፣ ከክህሎት ወይም ከእውቀት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው አግልገሎት ክፍያዎች ለምሳሌ ስልጠና፣ ከእቅድ ጋር የተያያዙ፣ የተለያዩ የጽሁፍ ዝግጅት፣ ለጥናቶች፣ ግኝቶችን ለማስተዋቅ፣ አዲስ ቴክኖሎጂ ወይም ፈጠራ ላይ ላተኮረ ተግባር

- **የዕለት ከዕለት ወጪዎች፡** ለተለያዩ ቁሳቁሶችን አገልግሎቶች የሚውል ለምሳሌ ግብዓት (ዘር፣ ማደበሪያ፣ፀረ-ተባይ፣ የቀን ሰራተኞች የጉልበት ዋጋ ወጪ) የሚያጠቃልል ሲሆን እንደ

አላቂ የቢሮ ቁሳቁሶች፤ ህተመቶችና በራሪ ጽሁፎች፤ ለማኑዋሎች፤ ለመጓጓዣ ወጪዎች (ትራንስፖርት፤ የመኝታና ውሎአበል፤ ለመገናኛና ለፍጆታ ወጪዎች (ዉሃ፤ ስልክ ኢንተርኔት፤ መረጃ ለማቀነባበር፤ ለቢሮ ዕዳት፤ ለጥበቃ አገልገሎትን) ያካትታል።

- **የእንቨስትመንት ወጪዎች** በምርቱ ላይ እሴት ለመጨር አስፈላጊ ለሆኑ አንስተኛ መሳሪያዎች (ገለፃ ለማድረግ ወይም ለማሳየት ብቻ)፤ ሊሰራ ከታቀደው ተግባር ጋር ቀጥተኛ ተዛማጅነት ላላው የቴክኒክ ድጋፍ ወይም ከክህሎት ጋር ለታያያዙ ውስን በጅት ሊያዝ ይችላል። አመልካቹ ይህ ወጪ ለፕሮጀክቱ ግብ መሳከት ምን ያህል አስተዋጽኦ እንደሚያደረግ ግልጽና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ማመላከት ይጠበቅበታል።

**ያልተፈቀዱ ወይም ብቁ ያለሆኑ ወጪዎች** በፕሮጀክቱ አይሸፈኑም። ሆኖም ግን አመልካቹ በራሱ የፋይናንስ ምንጭ ሊያወራርድ ይችላል። ለአብነት ያህል እነዚህ ወጪዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

- ከተፈቀደው ፕሮጀክት ጋር ቀጥተኛ ተዛማጅነት የሌለው ወጪ፤ በውልል ስምምነት ያልተካተቱ ተግባራት፤ ወይም ከፕሮጀክቱ ጋር ግንኙነት የሌለው ሥልጠና፤
- ከፍተኛ የካፒታል ወጪ የሚጠይቁ ለምሳሌ ታላላቅ የመስክ ማሽነሪዎች፤ የግንባታ መሳሪያዎች፤ ተሽከርካሪዎች፤ ግዙፍ የምርት ማቀነባበሪያዎችና የመያዣ መሳሪያዎች፤ ግንባታዎች (ህንፃ፤ ድልድይ፤ መንገድ)፤ የመሬት ግዢ፤ ከህግ ጋር የተያያዙ ወጪዎች
- ከውል ስምምነት በፊት የወጣን ማንኛውም ወጪ ለምሳሌ ዕዳ ለመክፈል፤ አስቀድሞ በሌላ የፋይናንስ ወጪ የተሸፈነን ለማካካስ የሚደረግ
- ለመንግስት መ/ቤቶች አስተዳደራዊ ወጪዎች
- ካፒታል ለመፍጠር የአክሲዮን ግዢ
- የምግብ፤ የሆቴል ወጪዎች፤ ስበሰባዎችን ለመሳተፍ የሚከፈል ወጪ ወይም ስጦታዎች
- በደረሰ አደጋ የጉዳት ወይም የካሳ ክፍያ በአደራዳሪዎች ሰምምነት ወይም በሌሎች ሁኔታዎች ቢወሰንም በዚህ ፈንድ አይስተናገድም ሆኖም በፈጻሚው አካል ሊሸፈኑ ይችላሉ።

### 3.6 ፈርጀ-ብዙ ጉዳች፤ ሥርዓተ ፆታና አካባቢ ጥበቃ

ፈረጀ-ብዙ ጉዮች በልማት ተገባራት ላይ ተጽዕኖ ሰለሚያሰድሩ ልዩ የፖሊሲ አቅጣጫ ስለሚያስፈልጋቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ አገሮች በእነዚህ ፖሊሲዎች ላይ አጠቃላይ ስምምነት

ደርሰዋል። የጾታ እኩልነትና የአካባቢ ጥበቃ በፕሮጀክት እቅድና ትግበራ ወቅት ትልቅ ተኩረት ከሚሹ ጉዳቾ በወነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው።

***ሥርዓተ-ጾታ***

በፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያን ምርምር ፈንድ በዋነኛነት ከያዛቸው ግቦች መካከል በሴቶችና ወንዶች መካከል አኩል የሆነ መብት፤ የስራ እድልና ግዴታ እንዲኖር ያበረታታል። ሴቶች በኢትዮጵያ በሰፊው በግብርና ዘርፍ ተሰማሪትው እንደመገኘታቸው መጠን በዚህ የፋይናንስ ድጋፍ ዋነኛ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይፈለጋል። ስለሆነም፤-

- በፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያን ምርምር ፈንድ በተመለከተ ከሚቃቃመው ኮሚቴ ውሰጥ ወሳኔዎችን በማሳረፍ ረገድ ሴቶች ቢያንስ 40% ሚና እንዲኖራቸው
- በሚቀረጸው የድርጊት መርሃ-ግብር የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ በወሳኛነት መካተት ያለበት ሲሆን ለአብነት ያህልም የሴቶች የሥራ ጫና፤ የሃብት ባለቤትነት፤ በአመራረር ጥብብ ስለጠና ወዘተ... ግምት ውስጥ መግበት ይኖርበታል፡፤የመደራድር ሃይል የመሳሰሉት
- የሴቶች የሥራ ፈጠራን ለማበረታታት ሲባል ከዚህ በፊት በምርምር የተገኙትን በማላመድና አቅም ግንባታ ተኮር ሥራዎችን በመስራት ይከናወናል
- ሴቶችና ተጠቃሚ ያለሆኑ የህብረተሰብ ክፈሎች በዚህ የድጋፍ ፈንድ ተጠቃሚ ለመሆን የፕሮጀክት ሃሳብ እንዲያቀርቡ የሚደገፉ ሲሆን ፕሮጀክቱም በኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳች ላይ ዘላቂነት ያለው የመልካም አስተዳደር፤ የፋይናንስ አቅም፤ የስራ እድል፤ ገበያ ተኮርና ትርፋማ ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት።

***የአካባቢ ጥበቃ***

የፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፕሮጀክት ሲተገበር የተፈጥሮ ሃበትንና የአካባቢ ንብረት ከሚያዛባና ከሚጎዳ ተግባር ነፃ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠይቃል። የሚቀርቡትን የፕሮጀክት ሃሳቦች ሲመረጡ በተፈጥሮ ሀብትና በህዝብ ላይ ጉዳት አለማድርሰ የሚለውን መርህ የተከተለ መሆን አለበት። ይህም በማህበረሰቡና በሥራው ላይ በሚሰማረው ግለሰብ ዘንድ ሊያደርስ የሚችለውን ችግር ማስወገድ ወይም መቀነስ ያስችላል። የሚቀርበውን የፕሮጀክት ሃሰብ የሚመረምሩ አካለት ፈረጀ-ብዙ ጉዳችን የሚከታተሉበት ዝርዝር ወይም ቅፅ (አባሪ 4) ከዚህ ማኑዋል ጋር ተያይዟል።

## 4. የፕሮጀክት ሃሳብ አቀራረብ ሂደት

አምለካቾች የፕሮጀክት ሃሳባቸውን በሚያቀርቡት ወቅት በሚያገኙት ገንዝብ በመጠቀም እንዴት እንደሚተገብሩት ዝርዝር የድርጊት መርሃ-ግብር ማያያዝ አለባቸው። አመልካቾች ሁለት ቅደም ተከተሎችን መከተል ይኖርባቸዋል። በመጀመሪያ አጠር ባለመልኩ የፕሮጀክቱን ንድፈ-ሃሳብ ማቀረብ የሚጠበቅባቸው ሲሆን ጽነሰ-ሃሰቡ በገምጋሚው አካል ተቀባይነት ያለው መሆኑን ሲገጽላቸው ወደ ዝርዝር የፕሮጀክት ዝግጅት የሚገቡበት ይሆናል። ይህ አሰራር በማዘጋጀት

የሚወስደውን ረጅም ጊዜና ወጪ ለመቀነስ ያግዛል ተብሎ ታስቦ ሲሆን የፕሮጀክት ሃሳቡም በጥራት እንዲቀርብ ሚና ይኖረዋል፡፡

**ቋንቋ**

የፕሮጀክት ንድፈ-ሃሳቡም ሆነ ሙሉ የፕሮጀክት ሃሳብ በአማርኛ ወይም በእንገሊዘኛ ሊቀርብ ይችላል፡፡ የአግሮቢግ ሴክረታሪያት ጽ/ቤት ከእሴት ሰንሰለት ድጋፍ ፈንድ ጋር የተያያዙ ሁሉንም መረጃዎች በአማርኛ እንዲወጡ ያደርጋል፡፡ ሁሉም የአማርኛ የፕሮጀክት ሃሳቦችና የኮሚቴ ስበሰባ ቃለ-ጉባኤዎቸ ለመረጃ ሲባል ወደ እንግሊዘኛ የመለሳሉ፡፡

## 4.1 የፕሮጀክት ንድፈ-ሃሳባ አቀራረብ ግንዛቤ መፍጠርና እንዲቀርብ ጥሪ ማስተላለፍ

በወረዳው የእሴት ሰንሰለት ድርጊት መርሃ ግብር የሚጣጣም ብቁ የሆኑ ማንኛውም አመልካቾች የፕሮጀክት ሃሳብ ሊያቀረቡ ይችላሉ፡፡ ሂደቱም፡-

**ሀ. ለማህበረሰቡ ስለፕሮጀክት ንደፈ ሃሳባ አቀራረብ ግንዛቤ መፍጠርና ጥሪ ማካሄድ፡** የእሴት ሰንሰለትን ለማሻሻል የቀረበ የፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያና ምርምር አገልግሎት የሚውል የፋይናንስ ምንጭ መኖሩን የግንዛቤ ፈጠራ መካሄድ ይኖርበታል፡፡ ዝርዝር የሆነ የገንዛቤ መፍጠሪያ ድርጊት መርሃ-ግብር በወረዳ የቴክኒክ ኮሚቴና ባለድርሻ አካላት የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡ የግንዛቤ ፈጠራው በሚመለከተው የወረዳ ጽ/ቤትና በአግሮቢግ ወረዳ አስተባባሪ የሚከናወን ሲሆን በዓመት አንድ ጊዜ ወይም እንደሁኔታው በተደጋጋሚ የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

አግሮ ቢግ የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳቦችን በየትኛውም ጊዜ (የጊዜ ገደብ ሳይኖረው) ይቀበላል፡፡ ለዚህም የሚያግዙና መረጃዎች፤ አጭር ስለፕሮጀክት አቀራረብ ጥሪና መመሪያና ወጥ የሆነ የፕሮጀክት ንድፈ-ሃሳብ ማቅረቢያ ቅጽ (አባሪ 1) በበቂ ሁኔታ ተባዝቶ ለሥራ ዝግጁ ሆኖ መቀመጥ አለበት፡፡

**ለ. የፕሮጀክት ሃሳብ እንዲቀርብ ጥሪ ለማደረግ መጋበዝ፡** የአግሮቢግ ፕሮገራም ድጋፍ ዩኒት ከወረዳ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የእሴት ሰንሰለትን እጥረቶችን ለመቅረፍ ሊሳተፉ የሚችሉ የመንግሰትና የግል ዘርፍ ተዋንያን መለየት ይጠቅበታል፡፡ በተጨማሪም አግባብነት ያለቸውን የአርሶ አደር አደረጃጀቶች፤ ማህበራት፤ የንግድና የምርምር ተቋማት በውል ተለይተው በአካለል በማነጋገር በቀረበው የፋይናንስ ምንጭ እንዴት አመልክተው መጠቀም እንደሚችሉ መታገዝ አለባቸው፡፡

የአግሮቢግ የወረዳ አሰተባባሪና የወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ ጋር በመሆን ለእሴት ሰንሰለት ድጋፍ ፈንድ የፕሮጀክት ሃሳበ ጥሪን ያስተላልፋሉ፤ እንደመረጃ ምንጭ ሆነው ያገለግላሉ፡ የፕሮጀክት ንድፈ ሃሰቦች እንዴት እንደሚጻፉ ያስረዳሉ ያግዛሉ፡፡ አስተባባሪው ማመለከቻዎችን ይቀበላል፤ እንዲጸድቁም ለቴክኒክ ኮሚቴው ያቀርባል፡፡

## 4.2 የቀረበን የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳብ መመርመርና ማጽደቅ

የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳብ ማመለከቻ ቅጽ አባሪ 1 ወጥ ሆኖ የተዘጋጀ ሲሆን አመለካቾች ፍላጎታቸውን የሚገልጹበትና ለገምጋሚዎች የሚረዳ መሰረታዊ መረጃዎችን የሚሰጥ ነው፡፡

አመልከቾች የፕሮጀክት ንድፈ-ሃሳባቸውን በቀጥታ ለወረደው አግሮቢግ አስተባባሪ መላክ አለባቸው፡፡ አስተባባሪውም የቀረቡለትን ማመልከቻዎች ሁሉ መዝገቦ በመያዝ ለወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡ የቴክኒክ ኮሚቴ አባለት ወይም ኮሚቴወው በሚሰይመው ቡድን የተሸሉትን ንድፈ-ሃሳቦች ለዚህ ተገባር በተዘጋጀው መገመገሚያ ወይም መለያ ቅጽ (አባሪ 2) በመጠቀም የተሻሉትን ይመረጣሉ፡፡ ለዚህም እንዲረዳቸው ከታች በተመለከቱት የመልመያ መስፈርቶች መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

- **የእሴት ሰንሰለት (ጥያቄ ቁጥር** 7) የፕሮጅከት ንድፈ-ሃሳብ በተመረጠው የእሴት ሰንሰለት ጋር ያተኮረ መሆኑና በአመልካቹ የተለየውን የምርቱን ችግር ወይም እጠረት ከመቅረፍ አንፃር ያለው ፋይዳ
- **የንግድ ልማት እቅድ (ጥያቄ ቁጥር** 8) የፕሮጀክት ሃሳቡ እጥረቱን ለመቅረፍ ምን አዳዲስ አሰራሮችን ይዟል፣ በፕሮጀክቱ ትግበራ አሁን ያለውን ችግር እንዴት እንደሚያስወግድ በመጨረሻም የሚገኘው መልክም ውጤት ምን እንደሆነ የሚያሳምን መሆን አለበት
- **የሚያመጣው አወንታዊ ተጽዕኖ (ጥያቄ ቁጥር** 11) ሊለካ የሚችል ውጤት ስለመኖሩ፣ ተጠቃሚው ማን እንደሆነ፣ የሚገኘው መልካም ዘላቂነትን ሁሉንም ባለድርሻ ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር

- **የአመልካቹ የመፈፀም ብቃት (ጥያቄ ቁጥር** 10) የቴክኒክ ችሎታ፡ አስተዳዳራዊ ብቃቱ፣ የፋይናንስ አቅም፣ የያዛቸው ስራተኞች የሥራ ልምድና ብቃት በመጠቀም ፕሮጀክቱን በአጋባቡ በመተግበራቸውና ግብን ከማሰካት አንፃር የሚመዘን ይሆናል፡፡

### ተወዳዳሪዎችን ማወዳደርና መምረጥ

እያንዳንዱ የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳብ በተመሳሳይ ጊዜ በሁለት ሙያተኞች ለየብቻ ነጥብ ይሰጣል፡፡ ከዚህ በታች በተመለከተው የመልመያ መስፈርት መሰረት ደረጃ ይሰጣሉ፡፡

| መስፈርት | የተሰጠው ክብደት /ሀ/ | በገምጋሚው የተሰጠ ወጤት (ከ10) /ለ/ | ውጤት /ሐ = ሀ X ለ/ |
|---|---|---|---|
| ከእሴት ሰንሰለት አንፃር | 30% | 8 | 2.4 |
| የንግድ ልማት ዕቅድ | 30% | 8 | 2.4 |
| ከሚያስከትለው አወንታዊ ተጽዕኖ | 20% | 7 | 1.4 |
| የተወዳዳሪው ብቃት | 20% | 5 | 1.0 |
| ድምር | 100% | | 7.2 |

ተወዳሪዎችን በመስፈርቱ አወዳድሮ ከመለይት በፊት የቴክኒክ ኮሚቴው የመስክ ጉብኝት ሊያደረግ ይችላል፡፡ የጉብኝቱም ዓላማ ገምጋሚዎች አመልካቾችን ከዚህ በፊት የማያውቋቸው ከሆነና በፕሮጀክት ንድፈ-ሃሳብ የቀረበው መረጃ ለማመሳከርና የመፈጸም ብቃታቸውን ለመፈተሽ ያገለግላል፡፡

**ብቁ ተወዳዳሪን ለይቶ ማጽደቅ**

የእያንዳንዱ ገምጋሚ አማካኝ ውጤት በየፕሮጀክት ንደፈ-ሃሳቡ ከተሰጠ በኋላ የሁለቱ ገምጋሚዎች ነጥብ ተደምሮ አማካኝ ውጤት ይደረሳል፡፡ በውጤቱ መሰረት የወረዳው የቴክኒክ ከሚቴ ለስትሪንግ ኮሚቴ የውሳኔ ሃሰብ ያቀርባል፡፡ ስትሪንግ ኮሚቴው ከ7 ነጥብ በላይ ያገኙትን ተስማምቶ ሊያጸድቀው ይችላል ካልሆነም ሌላ ውሳኔ ሊያሳርፍ ይችላል፡፡

## 4.3 የፕሮጀክት ሃሳብ አዘገጃጀት

በፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ ላይ የሚውለው መዋለ ነዋይ የሚጠበቀውን ውጤት ለማግኘት የተሻለውን የፕሮጀክት ሃሰብ ተቀብሎ ለማስተናገድ እንዲቻል በተቻለ መጠን ጥሩ የፕሮጀክት ሃሳብ እንዲቀርበ ከፍተኛ እገዛ ይሻሉ፡፡

**ለአመልካቾች የፕሮጀክት ሃሳብ አፃፃፍ ስልጠና መስጠት**

የፕሮጀክቱ ንድፈ-ሃሰብ ተቀባይነት እንዳገኝ አመልካቾች ስለዋናው ዝርዝር የፕሮጀክት ሃሰብ አቀራረብ ከ1-2 ቀናት የሚቆይ ስልጠና ለመስጠት በአግሮቢግ ወረዳ አስተባባሪ አማካኝነት ጥሪ

ይተላለፋል። ሥልጠናው ከሚያካትታቸው ርዕሶች መካከል መሰረታዊ የእሴት ሰንሰለት ፈንድ ግቦች፤ የተፈቀዱና የተከለከሉ የወጪ ርዕሶች፤ ስለፕሮጀክት ሃሳብ አዘገጃጀት መመሪያ (የፕሮጀክቱ አወቃቀር፤ የፕሮጀክት አፈቃቀድ ሂደት፤ የውል ሰነድ፤ የክፍያ አጠያየቅና ግዢ፤ ሪፖርት፤ ክትትልና ምዘና፤ ኦዲት ስለማስደረግና አግባብነት በሌላቸው ተግባራት ምክንያት ሊከስቱ ስለሚችሉ ጉዳችን ያጠቃልላል። ይህ ስልጠና ፈጠራ፤ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ የጋራ ግንዛቤ ይፈጥራል፡ ጥራት ያለው የፕሮጀክት ሃሳብ እንዲቀርብ እገዛ ያደርጋል፤ ትግበራውንም ያሳልጣል።

### ለፕሮጀክት ሃሰብ ዝግጅት የሚደረግ ሙያዊ እገዛ

ከስልጠና በኋላ አመልካቹ የፕሮጀክት ሃሳብና የስራ እቅድ ለማዘጋጀት በቂ አይደለሁም በሎ ካሰበ የወረዳው የቴክኒክ ኮሚቴ ሙያዊ እገዛ እንዲያደርግለት በስልጠና ወቅት ሊጠይቅ ይችላል። የወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ በስልጠና ወቅት ድጋፍ የሚሹትን መለየት ይጠበቅበታል።

### የፕሮጀክት ሃሳብ ዝግጅት

አመልካቾች በተዘጋጀው የፕሮጀክት ሃሰብ ማቅረበቢያ ቅጽ (አባሪ 3) በመጠቀም ማዘጋጀትና ማቅረብ ሃላፊነት አለባቸው። የፕሮጀክት ሃሰቡን ለመፍቀድ እንዲቻል የሚከተሉትን ጉዳዮች ምላሽ መስጠት የኖርበታል። የእሴት ሰንሰለት ችግሮችን ምላሽ የሚሰጥ መሆን አለበት፤ ሊመዘንና ሊቆጠር የሚችል ውጤት የሚያመጣ መሆን አለበት፤ ውጤቱ በመጨረሻ ሲመዘን በተጠቃሚዎች ዘንድ ተጨባጭ ለውጥ የሚያሳይ መሆን አለበት፤ በአባሪ 4 የተመለከቱትን ፈርጀ-ብዙ ጉዳዮችን በአጋባቡ መመለስ ይጠበቅበታል። አመልካቾች የተሟላ የፕሮጅክት ሃሳባቸውን ለአግሮቢግ አስተባባሪ ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን አስተባባሪውም መዝግቦ ለወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴ ያቀረባል።

## 4.4 ማጽደቅና አመልካቹ ውል እንዲወስድ ማሰወቅ

የፕሮጀክት ሃሳቡ እንደደረሰ የቴክኒክ ኮሚቴው የተወሰኑ አባለቱን የፕሮጅክት ሃሰቡን እንዲመረምሩ ሊመድብ ይችላል፤ አስፈላጊ ከሆነም የውጭ አማካሪዎችን ሊጠቀም ይችላል፤ ለውጭ አማካሪዎች የሚፈፀም ክፍያም በጀት ይያዛል።

### የቴክኒክ/የብቃት ፍተሻ

እያንዳንዱ የፕሮጀክት ሃሳብ በ3 ሙያተኞች በተናጠል በተመሳሳይ ጊዜ ወጥ በሆነ መስፈርት የመዘናሉ። በጨረሻም የ3ቱ ውጤት በአማካኝ ተሰልቶ በአባሪ 5 ቅጽ ተጠቃሎ ደረጃ ይሰጣቸዋል።

የማወዳደሪያ መስፈርቶች የሚከተሉት የሆናሉ

1) **የእሴት ሰንሰለት ፕሮጀክት ሃሳብ /ጥያቄ ቀጥር** 7/ ንድፈ-ሃሳብ በተመረጠው የእሴት ሰንሰለት ጋር ያተኮረ መሆኑና በአመልካቹ የተለየውን የምርቱን ችግር ወይም እጠረት ከመቅረፍ አንፃር ያለው ፋይዳ

2) **ፈጠራ/አዲስ አሰራር (ጥያቂ ቁጥር** 8) የፕሮጀክት ሃሳቡ በግልጽ በውስጡ ምን አዲስ ነገር እንደያዘ፤ በፕሮጀክቱ መጨረሻ ምዕራፍ አሁን ያለውን ችግር እንዴት እንደሚያሻሽላ ማመላከት አለበት፡፡

3) **የትግበራ ስልቱ /ጥያቂ ቁጥር** 9/ እቅዱን ተመጣጣኝ በሆነ ገንዘበና ሊጨበጥ የሚችል ውጤት በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ማሳካቱ

4) **የአመልካቹ የመፈፀም ብቃት (ጥያቂ ቁጥር** 10) የቴክኒክ ችሎታ፡ አስተዳዳራዊ ብቃቱ፤ የፋይናንስ አቅም፤ የያዛቸው ስራተኞች የሥራ ልምድና ብቃት በመጠቀም ፕሮጀክቱን በአጋባቡ በመተግበራቸውና ግብን ከማሰካት አንፃር የሚመዘን ይሆናል፡፡

5) **ከሚጠበቁት ተጨማሪ ጥቅሞች አንፃር / ጥያቂ ቁጥር** 11/ ከፕሮጀክት የሚጠበቁ ጥቅሞች በውል ተለይቶ መገለጽ አለበት፡፡ ከትግበራው ከወጣው ወጪ

6) **ከታላሚ ተጠቃሚዎች አንጻር /ጥያቂ ቁጥር** 12/ የእሴት ሰንሰለት ተዋንያን ከፕሮጀክቱ ተጠቃሚ መሆን አለባቸው፤ በተለይ ሴቶችና ወደጎን የተተው ድሃ አርሶ አደሮች ወይም አንስተኛ በለይዞታዎች ቅድሚያ ስለማገኘታቸው

7) **ከበጀት አንፃር /ጥያቂ ቁጥር** 13/ የቀረበው የማስፈጸሚያ በጀት ያልተጋነነና በመረጃ የተደገፈ የወጪ ግምት ሆኖ፤ በተለያዩ ርእሶች የተጠየቀው በጀት ከሥራው ጋርና ከሚጠበቀው ውጤት አንፃር የተጣጣመ መሆን አለበት፡፡

8) **ከመቀናጆ በጀት አንጻር /ጥያቂ ቁጥር** 14/ አመልካቹ የፕሮጀክቱን ምን ያህል ድርሻ በራሱ ገንዝበ (በጥሬ ገንዘብ) ለመሸፍን ይችላል ወይም ፍላጎተ አለው፡፡

9) **ሊሳኩ የሚችሉ አመላካቾች አንፃር /ጥያቂ ቁፅር** 15/ የሚጠበቁ ውጤቶች ሊለኩ ሊደረስባቸው የሚችሉ ሆነው ወደ ትግበራ ሲገባ እንዴት የእሴት ሰንሰለትን እንደሚያዳብርና ተጠቃሚዎች እነማን እንደሆኑ የሚገኘው ውጤት ዘላቂነት ያለውና አነስተኛ በለይዞታዎችን የሚጠቅም መሆን አለበት፡፡

10) **ፈርጀ-ብዙ ጉዳዮች - ሥርዓተ-ፆታ /ከመከታታያ ቅፅ** 1- 4/ ፕሮጀክቱ ሲታቀድ የሴቶችንና የወንዶችን ተሳፎ በደንብ ግምት ውስጥ ያስገባና ሥርዓተ-ፆታን እንደዋነኛ ስራ ብዕቅዱ ውስጥ ያካተተ መሆን አለበት፡፡

11) **ፈርጀ-ብዙ ሁኔታ ጉዳዮች- የአካባቢ እንክብካቤ / ከመከታታያ ቅፅ** 5-8/ የፕሮጀክተ ሃሰቡ ሲቀርብ የአካባቢ ደኅንነት በደንብ ግመት ውስጥ አስገብቶ የተዘጋጀ መሆን

አለበት፡፡ አስፈላጊ ከሆነና ተፅዕኖ የሚያስከትል ሆኖ ከተገኘ ችግሩን ለመቀነስ ያሰቀመጠው መፍትሄ በፕሮጀክት ሃሰቡ መታየት አለበት፡፡

**የመስክ ግምገማ**

አስፈላጊ ሲሆን የገምጋሚው ቡድን በፕሮጀክት ሃሳቡ የተካተቱ መረጃዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የመስክ ምልከታ ሊያካሂድ ይችላል፡፡ ለዚህም የፕሮጀክት ታላሚዎችን ወይም አመልካቾችን ቃለ-መጠይቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ሥርዓተ-ፆታን በዝርዝር መመልከት፡፡

**ፈርጀ-ብዙ ጉዳዮችን መገምገም**

ገምጋሚው ቡድን የሥርዓተ-ፆታና የአካባቢ ደህንነት ጉዳይ በፕሮጀክት ሃሰቡና በእቅድ ዝግጅት ወቅት በበቂ ሁኔታ መካተቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡ አስፈላጊ ከሆነም ተጨማሪ መወሰድ ያለባቸውን እርመጃዎች መከለስም ካለበት በውሳኔ ሃሰቡ መካተት ይኖርበታል፡፡

**ማደማደሚያና የውሰኔ ሃሳቦች**

በፈጠራ፣ሥርቶ ማሳያን ምርምር ድጋፍ ፈንድ የፋይናንስ ምንጭ የሚከናወን እንቨስትመንት በተቻለ መጠን በርካታ ቁጥር ላለው አርሶ አደር ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑንና ፕሮጀክቱም የፋይናንሰ አዋጭነቱ መረጋገጥ አለበት፡፡ የገምጋሚው ቡድን የፕሮጀክት ሃሳቡን በቴክኒክ ብቃቱና በሌሎች መመልመያ መስፈርት መመዘን ያለበት ሲሆን አስፈላጊ ከሆነም የሚሰጠው አስተያየት የትገበራውን ስልት ወይም በጀቱን እስከመቀይር ድረስ ሊሆን ይገባል፡፡

በመጨረሻም ገምጋሚው ቡድን የጠረጴዛና የመስክ ግመገማውን ካካሄደ በኋላ ለወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴ ማደማደሚያና የውሰኔ ሃሳቦች ያቀርባል፡፡

**አጠቃላይ ማደማደሚያ** ፡- በቀረበው የፕሮጀክት ሃሰብ ላይ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በቴክኒክ ዙሪያ ያለውን ድርሻ ግልፅና አጥር ያለ አስተያየት

**ምክረ ሃሳብ** ፡- የቀረበው ፕሮጀክት ሃሰብ የበቴክኒክ ኮሚቴው እንዲያጸድቀው ወደም ወደ አመለካቹ ተመልሶ ተከልሶ እንዲቀረብ ወይም ብቁ ባለመሆኑ ውድቅ መሆን እንዳለበት እንደሚያመላክተ ይጠበቃል፡፡

**የአግሮ ቢግ ስምምነትና የፕሮጀክትመፈቀድን ማሰወቅ**

የእያንዳንዱ ገምጋሚ አማካኝ ውጤት በየፕሮጀክት ንደፈ-ሃሳቡ ከተሰጠ በኋላ የገምጋሚዎች ነጥብ ተደምሮ አማካኝ ውጤት ይደረሳል፡፡ በተገኘው ነጥብ መሠረት ለእያነዳነዱ የፕሮጀክት ሃሰብ የማጠቃለያ ደረጃ ይሰጣል፡፡ በተገኘው ውጤትና ደረጃ መሠረት የወረዳው የቴክኒክ ኮሚቴ የውሳኔ ሃሳብ ለስትሪንግ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

የወረዳው ስትሪንግ ኮሚቴ የቀረበለትን የፈጠራ፣ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ የውሰኔ ሃሳብ ከተመለከተ በኂላ ሰትራቴጂካዊና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በመለየት፣ ከቦታ ወይም ከአካባቢ ምርጫ አንፃር፣ ከሚጠበቁ ውጤቶችና ከፋይናንስ አቅም ጋር አገናዝቦ የመጨረሻ ውሳኔ ያስርፋል፡፡

የወረዳው ስትሪንግ ኮሚቴ በመወከል የፕሮገራሙ ወረዳ አሰተባባሪ ብቁ ሆኖ የተመረጠውን አመልካች ያሳውቃል ያልተመረጡ ተወዳዳሪዎችም ሂደቱንና ውጤቱን እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡

## 5. ፕሮጀክት ትግበራ

### 5.1 ሕጋዊ የውል ስምምነት

የፕሮጀክት ሃሳቡ ተቀባይነት እንዳገኘ ወደትግበራ ይገባል፡፡ ወደትግበራ ለመግበት ፕሮጀክቱ ስለሚተገበርበት ሁኔታ በተመረጠው አመልካችና በፈንዱ ስክረታሪያተ መካከል ሕጋዊ የውል ስምምነት ይፈረማል፡፡ በሁሉም ፕሮጀከቶች ወጥ የሆነ የውል ስምምነት ቅጽ (አባሪ 6) እንዲኖር ታስቦ ናሙናው ከዚህ ማኑዋል ጋር አበሪ ሆኖ ተያይዟል፡፡

የፈንዱ ሴክረታሪያት ጽ/ቤት ፕሮጀክቱን ለመተግበር እንደተመረጠው አመልካች አቅም ሁኔታጋር ታይቶ ከትግበራ በፊት ስልጠና ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡ የስለጠናው ርዕስም በክፍያ አፈፃፀምን፣የግዢ ሥርዓት፣ በፋይናንስ አስተዳደርና ሂሳብ አያያዝ፣ በሪፖርት አዘገጃጀት፣ በኦዲትና በፕሮጀክት ክትትለና ምዘና ዙሪያ ይሆናል፡፡

### 5.2 የባንክ ሂሳብ ቁጥርና የክፍያ አፈፃፀም

ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገው ቅድሚያ ክፍያ ከመለቀቁ በፊተ ተጠቀሚው ድርጅት ቅድሚያ በአበቁተ በፕሮጀክቱ ስም ልዩ የባንክ ሂሳብ ቁጥር መክፈት ይጠበቅበታል፡፡ ከፕሮጀክቱ ጋር የተያያዘ ማንኛውም ክፍያ በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ብቻ የሚነቀሳቀስ ይሆናል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለሂሳብ ቁጥሩ ለብቻው የሂሳብ መዝገብ ከሌላ ጋር ሳይቀላቀል ይቋቋማል፡፡

### ቅድሚያ ክፍያ

ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ የሚለቀቀው ቅድሚያ ክፍያ እንደ ፕሮጀክቱ ባህሪ ዓይነት (ቅድሚያ ክፍያ የሚያስፈልገውና የማያስፈልገው መሆኑ ታይቶ) የሚለቀቅ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን የገንዘቡ መጠን ከ20% በላይ ሊሆን አይችልም፡፡

#### የገንዘብ ፍላጎት ሰንጠረዥና ክፍያ አጠያየቅ

የተመረጠው ድርጅት በትግበራ ወቅት በተለያየ ጊዜ የሚስፈልጋቸውን የገንዘበ ፍላጎት የሚያሳይ ሰንጠረዥ ከፕሮጀክት ሃሳቡ ጋር ተካቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ተከታታይ ክፍያዎች

ተጠቃሚው በጽሁፍ ጥያቄውን እንደሚያቀርብ የሚጠበቅ ሲሆን ከዚሁ ጋር ወቅታዊ የአፈጻጸም ሪፖርትና ለክፍያው አስረጅ የሆኑ ደጋፊ ሰነዶችን አያይዞ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

### የመጨረሻ ክፍያ

የፕሮጀክቱ የመጨረሻ ክፍያ (የፕሮጀክቱ ጠቅላላ ወጪ 5%) የሚለቀቀው ስለፕሮጀክቱ አፈፃፀም የማጠናቀቂያ ሪፖርት ተዘጋጅቶና ለፈንዱ ሴክረታሪያት ቀርቦ፤ ከፕሮጀክቱ ጋር የተያያዘ ማንኛውም የተንጠለጠሉ ጉዳዮች ሁሉ እልባት አግኝተውና የፕሮጀክቱ ፋይል ከተዘጋ በኋላ ይሆናል፡፡

## 5.3 ግዢ

የፕሮጀክቱ ተግባሪ ድርጅት ከተፈቀደው ፕሮጀክት ላይ ግዢ ሊያከናውን ይችላል፡፡ ግዢ በሚፈጸምበት ወቅት ሥራ ላይ የሚውለው የክልሉ መንግስት በሚከተለው የግዢ ሥርዓት ይሆናል፡፡ የፈንዱ ሴክረታሪያት ጽ/ቤት ፈፃሚዎች የሚመሩበት የግዢ ማኑዋል ያዘጋጃ ሲሆን ለትግበራም እንዲያግዝ ለሚመለከታቸው ሙያተኞች ስልጠና ይሰጣል፡፡

### ከገዢ በፊት የአግሮቢግን ስምምነት ማግኘት

የፕሮጀክት አስፈጻሚው የግል ተቋም ከሆነ የግዢ ውል ከመያዙና ግዢ ከመፈጸሙ በፊት ስለተከተለው የግዢ ሥርዓት ከመንግሰት የግዢ ህግ አንፃር መታየት ስላለበት ከፈንዱ ሴክረታሪያት ወይም የወረዳውን አግሮቢግ አሰተባባሪ ስምምነት ማግኘት አለበት፡፡

## 5.4 የፋይናንስ አስተዳድርና የሂሳብ አያያዝ

የፈንዱ ተጠቃሚ ድርጅት ተገቢና ግልጽ የሆነ የፈንድ አሰተዳደር የመዘርጋት ሃላፊነት አለበት፡፡ በአተገባበር ላይ ብክነት ወየም ያልተፈቀደ ክፍያ ተፈፅሞ ቢገኝ ለፕሮጀክቱ የሚለቀቀው ገንዘብ እንዲቋረጥ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ አግባብነት የሌለው ወጪ ተፈፅሞ ቢገኝ ለፕሮጅከቱ ገንዘቡ ተተክቶ ወጪው በፈፃሚው ድርጀት የሚሸፈን ይሆናል፡፡

### የሂሳብ አያያዝ

ለእያንዳንዱፕሮጀክት ከሌላ ሂሳብ ጋር ሳይቀለቀል ለብቻው ተገቢ የሆነ የገቢና ወጪ መዝገብ ይቋቋማል፡፡ ተፈላጊ መረጃዎች በሙሉ በሂሳብ መዝገቡ መሞላት ያለባቸው ሲሆን ለምዝገባ መነሻ የሆኑ የሂሳብ ሰነዶች (የግዢ ማዘዣዎች፤ ደረሰኞች፤ አቅራቢዎች የተለዩበት ማብራሪያ… ወዘተ) በአስረጅነት መያያዝ አለባቸው፡፡

የፕሮጀክት ተገባሪው ድርጅት አሰቀድሞ በተፈረመው ውል መሰረት የሂሳብ መግላጫ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት ይጠበቅበታል፡፡ ከፕሮጀክቱ ጋር የተያያዘ ማንኛውም መዝገብ፤ የሂሳብ

መግለጫ ሪፖርቶች፤ ደጋፊ የሂሳብ ሰነዶች፤ ወዘተ... ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀና አግሮቢግ ሂሳቡን አስመርምሮ የኦዲት ሪፖርት ከወጣ በኋላ ቢያንስ ለ3ዓመታት በአግባቡ ጠብቆ ማቆየት አለበት፡፡

## 5.5 የሩብ ዓመት ክንውን ሪፖርት

የፈንዱ ተጠቃሚ ድርጅት **በአባሪ 7** ቅጽ መሰረት የየሩብ ዓመት የተሟላ የአፈፃፀም ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡ ሪፖርቱ ለወረዳው አስተባባሪ የሚሰጥ ሆኖ አስተባባሪው የሁሉንም አዘጋጅቶ ለውረዳው የቴክኒክ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡ ኮሚቴውም የራሱን አስተያየት አካቶ ለወረዳው ስትሪንግ ኮሚቴ ይለካል፡፡

## 5.6 የፋይናንስ ሪፖርት

በተመሳሳይ በየሩብ ዓመቱ የመጨረሻ ወር ላይ የፕሮጀክቱን የገቢና የወጪ ሪፖርት አዘጋጅቶ መላክ ይጠበቅበታል፡፡ የፕሮጀክቱ ቀጣይ ሩብ ዓመት የሚያስፈልገው ገንዘብ የሚለቀቀው ያለፈው ሩብ ዓመት የፋይናንስ ሪፖርት ሲቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡ የፋይናንስ ሪፖርቱ ከሥራ ክንውን አፈፃፀም ሪፖርት ጋር ተያይዞ መላክ አለበት፡፡

የየሩብ ዓመቱ የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ **አባሪ 8** ከዚህ ማኑዋል ጋር የተያያዘ ሲሆን የፕሮጀክቱ የተፈቀደው በጀት በየንኡስ እርዕስና የወጪ ሂሳብ መደብ ይሞላል፡ የባለፉት ሩብ ዓመታትና የወቅቱ ሩብ ዓመት ወጪ በተዘጋጀላቸው ቦታ የሞላል፡ ከተፈቀደው ጠቅል በጀት እስካሁን የወጠጣውን የወጪ ድምር በማቀናነስ ድርጅቱ ያልተጠቀመበትን ወይም ሥራ ላይ ያልዋለውን በጀት ያገኛል፡፡

## 5.7 ክትትልና ቁጥጥር

የወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴና የወረዳው አስተባባሪ ፕሮጀክቶች እንዴት እየተከናወነ እንደሆነ ወደመስክ እየተወጣም ተከታታይ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

### በመከናወን ላይ ያሉ ፕሮጀክቶችን ክትትል ማድረግ

የወረዳው አሰተባባሪ በመከናወን ላይ ያሉ የሁሉንም ፕሮጀክቶች ሪፖርት በመረከብ ምዝገባ በማከሄድ አፈፃፀሙን ከዕቅዱ ጋር ያነፃጽራል፡፡ በመቀጠልም

1) የፋይናንስ ሪፖርት በትክክል መዘጋጀቱንና አስፈላጊ ደጋፊ ሰነዶች መያያዛቸውን ያረጋግጣል

2) ከፈንዱ ተጠቃሚ በደረሰው የቅድሚያ ክፍያ ጥያቄ መሰረት በቀጣይ 3 ወራት የሚያስፈልገውን ገንዝብ በማዘጋጀት ለሴክረታሪያት ጽ/ቤት ይልካል

3) አጠቃላይ የፕሮጀክትን አፈፃፀም በተለይ ከእቅዱ አንፃር የሚያሳይ አጠር ያለ የማጠቃለያ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

የወረዳ አስተባባሪው በትግበራ ላይ አፋጣኝ ምላሽ የሚሹትን ጉዳዮች ወዲያውኑ ምላሽ መስጠት ያለበት ሲሆን ችግሮችን መከነመፍትሄ ሃሰቦቻቸው ጋር ለውዳው ቴክኒክ ኮሚቴም ያሳውቃል፡፡

## የመስክ ክትትል

የወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴው ሀሉንም ፕሮጀክቶች መስክ በመውጣት የሚጎበኝበትን ጊዜ አስቀድሞ እቅድ ያወጣል፡፡ የመስክ ጉብኝት የሚያደረገው ቡድን አባላትም የወረዳው አስተባባሪና ከቴክኒክ ኮሚቴው አባለት መካክል ወይም አገልገሎት ከሚሰጡ የውጭ አካላት በመመደብ ይሆናል፡፡ የመስክ ጉብኝቱ ሳይቆራረጥ ማከናወን ያስሰፈለገበት ዋናው ምክንያት

- የፋይናንሰ አሰተዳደሩና አደረጃጀቱ ትክክል መሆኑንና ሥራ ላይ የዋለው ገንዘብ በትክል ሪፖርት መደረጉን ለማረጋገጥ
- የተከናወነው ተግባር ይከናወናል ተብሎ ከታሰበው አንፃር ምን ያህል እንደሆነ ለማጣራትና ለሚቀጥለው ሩብ ዓመት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለመልቀቅ የሚስችል ሁኔታ እንዳለ ለመፈተሽ ነው፡፡

በትግበራዉ የመጀመሪያ ጊዜ ክትትል ማድረግ ሥራ ላይ የዋለው ገንዝብ በስምምነቱ ለተጠቀሱ ተግባራት ላይ መዋሉንና ግዢዎች ስርዓቱን ጠብቀው የተከናወኑ ለመሆኑ ለማረጋገጥ ይጠቅማል፡፡

### የፕሮገራሙን የፋይናንስ አስተዳደር ማኑዋል ባለመተግበር ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳዮች

የፈንዱ ተጠቀሚ ድርጅቶች ይህን ማኑዋል ባለማከበራቸው በመጀመሪያ የሚወሰድው እርምጃ የሚቀጥለውን ሩብ ዓመት የሚለቀቅ ገንዝብ ሊያሰርዝ ችላል፡፡ ቀጥሎም በጉዳዩ ላይ በቂ ማብራሪያ ካልተገኘ ልዩ የሂሳብ ኦዲት እንዲከናወን ይደረጋል፡፡ አሁንም ከፕሮጀክት ተጠቃሚው ወገን በቂ ትብብር ካልተገኘ ተጨማሪ ጉዳት ከማስከተሉ በፊት ወዲያዉኑ ፕሮጀከቱ እንዲቋረጥ ይደረጋል፡፡ በዚህ ሂደት ወንጅል የተፈጸመ ከሆነ፤ የፕሮጀክቱ ገንዘብ ባክኖ ከተገኘ ገንዘቡ እንዲተካና በአጥፊዎችም ላይ በፈፀሙት እመንት ማጉደል የፈንዱ ሴክረታሪያት ክስ ሊመሰርት ይችላል፡፡

## 5.8 የማጠናቀቂያ ሪፖርትና ፕሮጀክትን መዝጋት

ፕሮጀክትን በአግባቡ ማጠናቀቅና መዝጋት ተገቢ ነው፡፡ አንድ ድርጅት ሲያካነውን የቆውን ፕሮጀክት ከመዝጋቱ በፊት ያልተጠናቀቁ ምዝገባዎች፤ በሚመለከተው አካል ያልፀደቁ በፕሮጀክቱ የተገኙ የስራ ውጤቶችና ያልተጠናቀቀ የፋይናንስ ጉዳዮች በሙሉ በተገቢው መልኩ መጠቃለል ይጠበቅባቸዋል፡፡

እንዲሁም ባልተጠናቀቁም ሆነ በሌሎች ጉዳዮች ላይ ከፕሮጀክት ፈጻሚው ጋር መልካም የስራ ትብብር እንዲኖር ለማስቻል የመጨረሻ የፕሮጀክቱ 5% ክፍያ የማጠናቀቂያ ሪፖርት ከተዘጋጀና ከቀረበ በኋላ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

### የማጠናቀቂያ ሪፖርት

ፕሮጀክቱን ሲያከናውን የቆየው ድርጅት ለዚህ ሲባል በተዘጋጀው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ የሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ በአባሪ 10 መሠረት አዘጋጅቶ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ የሪፖርቱ ይዘትም ያለፉትን ሩብ ዓመታዊ ሪፖርቶችን አጠር አድረጎ አጠቃሎ ያያዘ፤ በፕሮጀክቱ የውል ስምምነት በተጠቀሱ ዋና አማላካቾች መሠረት የተገኙ ውጤቶች የዳሰሰ መሆን ይኖርበታል፡፡

### ፕሮጀክቱን መዝጋት

በወረዳ ደረጃ ፕሮጀክቶችን ለመዘጋት የሚያስፈለገውን መድረክ የማዘገጀት ሃላፊነት የወረዳው የቴክኒክ ኮሚቴና የውረዳ አግሮቢግ አስተባባሪ ድርሻ ነው፡፡ ፕሮጀክቱን ለመዝጋት ከሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች መካከል

1) አንድ ወይም በርካታ የሆኑ ከተወሰኑ ባለድርሻ አካላት ጋር ተኮር ውይይት ማከሄድ /አባሪ 11/ በመጠቀም
2) ከፕሮጀከቱ ውጤት ተጠቃሚዎች ያገኙትን ጥቅም በምስክርነት ማሰባሰብ /አባሪ 12/
3) ሁሉም ያልተከፈና የተጠለጠሉ ሂሳቦች መከፈላቸውን፤ ሥራ ላይ ያልዋለ ገንዘብ መመለሱን በማረጋገጥ ሂሳብን መዘጋት
4) ከፕሮጀክት አሰፈጻሚው የቀረበውን የማጠናቀቂያ ሪፖርት ማጽደቅ
5) ኦዲት በማስደረግ ግድፈት የሌለበት የኦዲት አስተያየት ሪፖርት መቀበል
6) የፈንዱ ሰክረታሪያት ለፕሮጀክት ፈጻሚው አካል ፕሮጀክቱ ስለመዘጋቱና ሁሉም ተፋላጊ ነገሮች መሟላታቸውን የሚገልጽ ደበዳቤ መፃፍ፤ ከዚህ በኋላ የሂሳብ ሰነዶች ለመንግሰት ኦዲት ቢያነስ ለ3 ዓመት መጠበቅ እንዳለባቸው ማሳወቅ
7) ቀሪውን የመጨረሻ የፕሮጀክቱን 5% ክፍያ እንዲፈፀም ማደረግ ይሆናል፡፡

## 6. የማጠናቀቂያ ሂሳብ ምርመራ (ኦዲት)

የተሰጠው የፕሮጀክት ድጋፍ ፈንድ የህዝብ ሀብት እንደመሆኑ መጠን አስቀድሞ በተደረሰው ስምምነት መሠረት ገንዘቡ በአገባቡ ሥራ ላይ ስለመዋሉና የሂሳብ አያያዙ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡

የፈጠራ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድን ሂሳብ ምርመራ ፕሮጀክቱ እንደተዘጋ ወዲያወኑ የሚከናወን ሲሆን በመንግስት ወይም አገልገሎቱን በሚሰጡ በሌላ የውጭ ኦዲተሮች እንዲመረመር የፈንዱ ሰክረታሪያት ጽ/ቤትና የወረዳው ስትሪንግ ኮሚቴ ሃላፊነት አለባቸው፡፡

በፈጠራ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ ትግበራ የተዘጋን ፕሮጀክት ኦዲት ማስደረግ ከሚከናወኑት ሥራዎች መካካል አንዱ ነው፡፡ ሂሳቡን ለማሰመርመር የሚስፈለገውን የአገለግሎት ክፍያ የሚውል በአግሮቢግ የፕሮገራም በጀት ይያዛል፡፡ ምርመራው በፋይናንስ ጉዳዮች የተጣራ መረጃ ከመስጠቱም ባሻገር በፕሮጀክቱ ከተቀመጡት ዋና ዋና አመላካቾች አንፃርም የተገኘው ውቴትም የሚረጋገጥበት ዘዴ ነው፡፡

### የሂሳብ ሰነዶችን ጠብቆ ስለማቆየት

ማንኛውም የፕሮጀክቱ የፋይናንስና የግዢ ሰነዶች ፕሮጀክቱ ተዘግቶና ኦዲት ተደርጎ የኦዲት ሪፖረቱ ከወጣ በኋላ ቢያንስ ለ3ዓመት በመንግስት አካል ለሚደረግ እንስፔክሽን/ኦዲት ክፍት ሆኖ መጠበቅ የኖርበታል፡፡

## 7. የፕሮጀክት ውጤትን መመዘንና የመጣውን ተፅዕኖ መዳሰስ

**ውጤት**፡ ከፕሮጀክቱ በዋጋ ሰንሰለት ላይ ተከስተው ለነበሩ እጥረቶች ተጨባጭና መሰረታዊ ለውጦች ወይም መፍተሄ የሚጠበቅ ሲሆን እነሱም አዲስና የተሞከረ የአሰራር ዘዴ መምጣቱ፤ የተሞከረ የድህረ-ምርት አያያዝና ብክነትን የቀነሰ ስልት ሰለመገኘቱ፤ የተሻሻለ የማቀነባበርና የአሰተሻሸግ ዘዴን ያመጣ ሥለመሆኑ፤ ገበያን የሚያበረታታና የሚያስፋፋ ሃሳብና የመሳሰሉት ከሚጠበቁ አይነተኛ ለውጦች ናቸው፡፡

በዚህ ፕሮጀክት የተገኙ ለውጦች አግሮቢግ በሌሎች ክፍሎች አሳካቸዋለሁ ብሎ ከያዘቸው ተግባራት ጋር መተሳሰር ያለባቸው ሲሆን ለምሳሌ አንስተኛና ከንግድ ጋር የተሳሰረ የግብርና እንቨስትመንት ማሰፋፋትና ይህም ቀጣይነቱን ይዞ መዝለቁን በዚህም በረጅም ጊዜ የአንስተኛ ባለይዞታዎች ዘንድ ድህነትን መቀነስ ከሚለው ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት፡፡

**ከፕሮጀክቱ የሚጠበቀው አወንታዊ ተጽዕኖ የሚረጋገጠው** በግብርና ላይ የተሰማሩ አነሰተኛ ባለይዞታዎች በእሴት ሰንሰለት ፕሮጀክት በመሳተፍ የግብርና ምርትን ከገበያ ጋር በማተሳሰር በድህነት ቅነሳ የታየው ለውጥ ነው፡፡ በረጅም ጊዜ የሚታዩ መልካም ተፅዕኖዎች የሚረጋገጡት የገበሬዎች ምረታማት በከፍተኛ ደረጃ በማደጉ፤ ገቢያቸው በከፈትኛ ደረጃ ሲሻሻል፤ ምረታቸውን በተሻለ የመሻጫ ዋጋ ሲሸጡና በእሴት ሰንሰለት ተግባር ላይ የተሰማሩ ደርጅቶች ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ ነው፡፡ በዋጋ ሰንሰለት የሴቶች ተሳትፎ በከፍተኛ ደረጃ ይሻሻላል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በረጅም ጊዜ በፕሮጀክት ትግበራ ምክንያት የመጡ መሰረታዊ ለውጦችና እድገት የሚታየው ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀ በዃላ ነው፡፡

**አወንታዊ ለውጦችን ለመፈተሽ የሚረዱ አመላካቾች**፡ በፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያን ምርምር ድጋፍ ፈንድ የመጣ መሰረታዊ ለውጦች በእያንዳንዱ ፕሮጀክት በተናጠል በአጭር ጊዜና በመካከለኛ ጊዜ በተገኙ ውጤቶች ይለካል፡፡

**የፈጠራ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ ውጤት ክክትትልና ምዘና አንፃር የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ**




**የፈጠራ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድን ወጤት /Result/ መለካት**

የፈጠራ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድን ሂደት አሃዛዊ መለኪያዎች በቴክኒክ ኮሜቴው የሚሰበሰብ ሲሆን የአግሮቢግ ወረዳ አስተባባሪም እገዛ ያደርጋል፡፡ መረጃው በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት ይደረጋል፡፡ የሚሰበሰበው መረጃ

1. የቀረበ የፕሮጀክት ንድፈ ሃሰብና የፕሮጀክት ሃሳብ ቁጥር
2. አማካኝ ክበደት ዋጋ የተሰጠው የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳብ (ከተገመገመው ፕሮጀክት ሃሰብ ቁጠር ጋር)
3. አማካኝ ክበደት ዋጋ የተሰጠው የፕሮጀክት ሃሳብ (ከተገመገመው ፕሮጀክት ሃሰብ ቁጠር ጋር)
4. የፈጠራ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ ማመልከቻዎች ተቀባይነትና ሊለካ ከሚችል አመላካች ውጤታማ አፈፃፀም ያሳዩ ፕሮጀክቶች መቶኛ ድርሻ (ከፕሮጀክት ሃሳብ ጥያቄ ቁትር-15)
5. በየሩብ ዓመቱ በተፈቀደ የድጋፍ ፈንድ ተከፈለ የገንዘብ መጠን ከሩብ ዓመቱና ካለፉት ሩብ ዐመታት መቶኛ ድርሻ
6. ለግሉ ዘርፍ ከፈጠራ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ የተሰጠ ፕሮጀክት መቶኛ ድርሻ

7. የተፈቀድ የፕሮጀክት ሃሳብ እና በከፍተኛ ደረጃ ፈጠራ የታየበት ፕሮጀክት ቁጥርና መቶኛ ድርሻ (የፕሮጀከት ሃሰብ መገምገሚያ መስፍረት ጥያቄ ቁጥር- 7 ለ)

8. በፈጠራ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ በተሰጠ ድጋፍ የተሳተፉ የሴቶች መቶኛ ድርሻ

9. በተፈቀደው ድጋፍ ልዩ መፍትሄ ይዘው የመጡ ፕሮጀክቶች ቁጥር (ከፕሮጀከት ሃሳብ ጥያቄ ቁትር- 7)

2. በፈጠራ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ የተገኘን ውጤት ጥራት መዳሰስ (አሃዘዊ ባልሆኑ መለኪያዎች) Qualitative Assesement of VCF results (መረጃው በእያንዳንዱ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ ከዚህ በታች በተመለከተው መሰረት ሊጠናቀር ይችላል፡፡

- **ቡድን ተኮር ወይይት ማከሄድ /አባሪ** 11/ አባላት በፕሮጀከት ሃሳባቸው ያሰቀመጡትን ዓላማ ማሳካታቸውን በጋራ እንዲወያዩ እድል ለመሰጠት ሲሆን ምናልባት አላማቸውን ካላሳኩ ለዚህ ችግር ምን ምክንያቶች እንደነበሩ በጋራ የሚፈትሹት ይሆናል፡፡ ከዚህም ባሻገር ከሂደቱ ምን ተሞክሮ እንዳገኑ፤ በሌላ በተለየ መልኩ እንዴት ቢሰራ ኖሮ የተሸላ ውጤት ይገኝ ነበር በሚለው ወይይት ይደረጋል፡፡ ቡድኑ ከሂደቱ ለአባላት ምን ጥቅም እንዳስገኘ በተለይም የተሻለ ምርት ከማምረት አንፃር፤ ጥሩ የመሻጫ ዋጋ በማግኘት ረገድ፤ ኪሳራን በመቀነስ በኩል ወይም የተገኘ ተጨባጭ ጥቅም አንፃር ዳሰሳ ይደረጋል፡፡ በተመሳሳይ ቡድኑ የዋጋ ሰንሰለት ፈንድ በመጠቀም ምክንያት በመሰረታዊነት ምን የተለየ ውጤት እንደተገኘ ፍተሻ ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ ጉዳዮች በአግሮቢግ ክትትልና ምዘና አባላት በሚያጠናቅሩተ ሪፖርት የሚካተት ይሆናል፡፡

- **የተጠቃሚዎችን ምስክርነት ማሰባሰብ /አባሪ** 12/ ከተወሰኑ የቡድን አባለት ጋር ሰላሳለፉት ልምዳቸው የጠለቀ ውይይት ማከሄድ ሲሆን በተቻለ መጠን አባላት ሲመረጡ ሁሉንም አባላት ሊወክሉ ስለመቻላቸው እርግጠኛ መሆን ይጠይቃል፡፡ በዚህ ውይይት ላይ አባላት በግለሰብ ደረጃ ያገኙትን የተጠቀሙትን ፊት ለፊት ምስክርነታቸውን እንዲሰጡ ማድረግ ነው፡፡ ተሳታፊዎች ለማመስገን ሳይሆን በተክክል የተገነዘቡትን አሰተያየታቸውን እንዲሰጡ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ ውይይቶች (ታሪኮች) ከመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ የተገኙ የተማርናቸው ተሞክሮዎች ተብለው በአግሮቢግ ክትትልና ምዘና አባላት ሪፖርት የሚካተት ይሆናል፡፡

በሁለቱም ዘዴ የተገኙ ጠቃሚ መረጃዎች የፕሮጀክቱን ውጤት ለመተንተን እንደግብዓት ሆኖ ከማገልገሉም በላይ በፕሮጀክቱ ማጠቃለያ ሪፖርት ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል፡፡

### 3. አሃዛዊ የእሴት ሰንሰለት መረጃ

ይህ መረጃ ከሂሳብ ምርመራ ሪፖርት ማግኘት የሚቻል ሲሆን ከሚፈለጉት መረጃዎች መካከል

10. የየድርጅቶች የሽያጭ ምልልስ

11. የሽያጭ ምልልስ ከተለያዩ እሴት ሰንሰለት አንፃር

12. ለእያንዳንዱ አባላት ከእሴት ሰንሰለት የተከፈለ የገንዘብ መጠን

13. የግብዓት ሽያጭ

14. በየማህበራት ያለው የአባለት ብዛት /ሴት ወንድ ድምር/

15 በየማህበራት ያለው ቋሚ ሰራተኛ ብዛት /ሴት ወንድ ድምር/

4. የአግሮ ቢግ ምዘናና ክትትል ቡድን **የአባለት እርካታ ዳሰሳ ጥናትና ሌሎች ጥናቶችን** ተጨማሪ መረጃዎች ሲፈልግ  ሊደርግ ይችላል፡፡ የፈጠራ፤ ሥርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ ስኬት አማላካች ከሆኑት መካከል የተጠቃሚዎች በፕሮጀክቱ ያገኙት እርካታ፤ እምነት፤ የፋይናንስ ምንጭ ተደራሽነት በቀላሉ ሲገኝ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

16. በእሴት ሰንሰለት የሚሳተፉ አካላት በግብዓት፤ በኤክስቴሽን፤ በንግድ፤

በእንቨስተምነት፤ ተለያዩ እደሎችን በመጠቀም ያላቸው እርካታን እምነት

17. እነዚህ አካላት በትርፋማነት፤ በገበያ ላይ ያለ ፍላጎትና የተረጋጋ ገበያ  በመኖሩ

ምክንያት ያገኙት እምነትና እርካታ

አግሮቢግ ሁሉንም የተሳተፈባቸው ተጋባራትና የተገኙ ውጤቶች ላይ  በየዓመቱ ትንትና ያዘጋጃል፡፡ ለምሰሌ በዋጋ ሰንሰለት ድጋፍ የተገኙ ውጤቶች ከአግሮቢግ አስተዋጽዖ አንጻር ይጠናል፡፡ ሪፖርቱም በፕሮገራሙ አመታዊ የክትትልና ምዘና ሪፖርት የሚካተት ይሆናል፡፡ የፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ ትግበራ ከአጠቃላይ የአግሮቢግ ከሚጠበቅ ውጤት ጋር ይመዘናል፡፡

**የፕሮገራሙ ወጤት አማላካች**

18. በፈጠራ፤ ሰርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ ዘላቂነት ያለው ፈጠራና

እንንስተምነት የተሰጠ ድግፍ በቁጥርና በመቶኛ

## አባሪ 1፡ የፕሮጀክት ንድፈ-ሃሳብ ማቅረቢያ ቅፅ

የፈጠራ፤ ሰርቶ ማሳያን ምርምር ድጋፍ ፈንድ

(እባክዎትን ሁሉንም ጥያቄዎች ይመልሱ)

1. **የአመልካቹ ስምና አድራሻ**

2. **ስለ አመልካቹ አጭር መግለጫ፡ ሀ)** ህጋዊ ሰውነት፤ ለ) የተሰማራበት የሥራ መስክ፤ ሐ) ባለፉት 3 ዓመታት ያንቀሳቀሰው የሃብት መጠን ፤ መ) የያዘው የሰራተኛ ብዛት

3. **ድርጅቱን ወክሎ ግንኙነት የሚያደርግ ሰው** ሀ) ስም ለ) በመ/ቤቱ ያለው ሃላፊነት ሐ) አድራሻ መ) ስልክ ቁጥር ሠ) ኢሜል

4. **የፕሮጀክቱ መጠሪያ ስም**

5. **ፕሮጀክቱ የሚገኝበት ቦታ (ወረዳ ቀበሌ)**

6. **ፕሮጀክቱ የሚተገበርበት ጊዜ**

7. **ፕሮጀክቱ ምን የተለየ ችግር ለመፈታት ነው እየሞከረ ያለው?** የተለዩትን ችግሮች ወይም እጥረቶች ምላሽ በመስጠት ምን ያህል አግባብነት አለው?

8. **የፕሮጀክቱ ፈጠራ /አዲስ ሥራ** በፕሮጀክቱ ላይ ፈጠራ የሚያሰኘው ምንድን ነው?

9. **የሚከናወኑ ተገባራት፡** ፕሮጀክቱን ለመተግበር የሚከናወኑ ተግባራት

10. **ፕሮጀክቱን ለመተግበር ድርጅቱ ያለው ብቃት፡ ሀ)** ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ሥራ ያለው ልምድ፤ለ) ወደ ሥራ የሚያሰማራቸው ሰራተኞች የትምህርት ዝግጅት ሐ) የፕሮጀክት ፋይናንስ አስተዳደርና ሪፖርት የማዘጋጀት ብቃት

---

11. **ከፕሮጀክቱ የሚጠበቁ ተጨማሪ ጥቅሞች ፤ ውጤቶችና ተጠቃሚዎች፡** ሀ) አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ከፕሮጅክቱ ትግበራ የሚገኝ ጥቅም ይገለጽ ለ) ተጠቃሚዎች እነማን እንደሆኑ ይጠቆሙ

---

12. **የሚያስፈልግ የገነዘብ መጠን፡** ፕሮጀክቱን ለመተግበር የሚያስፈለገው በጀት

ማሳሰቢያ

ከ3 ገጽ በላይ ባይሆን ይመረጣል

ለወረዳው ወግሮቢግ አስተባባሪ የሚሰጥ

## አባሪ 2፡ የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳብ መገምገሚያ ቅጽ

**የፈጠራ፤ ሰርቶ ማሳያን ምርምር ድጋፍ ፈንድ**

(እባክዎትን ሁሉንም ጥያቄዎች የመልሱ)

---

1. **የፕሮጀክት ማመልከቻ ቁጥር፡**

---

2. **የአመልካቹ ስም፡**

---

3. **የፕሮጀክቱ ርዕስ፡**

---

4. **ድርጅቱን ወክሎ ግንኙነት የሚያደርግ ሰው፡**

---

**የመመልመያ መስፈርት፡**

**ሀ) የእሴት ሰንሰለት (ጥያቄ ቁጥር 7)** የፕሮጅክት ንድፈ-ሃሳብ በተመረጠው የዋጋ ሰንሰለት ጋር ያተኮረ መሆኑና በአመልካቹ የተለየውን የምርቱን ችግር ወይም እጠረት ከመቅረፍ አንፃር ያለው ፋይዳ

**ለ) ፈጠራ/አዲስ አሰራር (ጥያቄ ቁጥር 8)** የፕሮጀክት ሃሳቡ በግልጽ በውስጡ ምን አዲስ ነገር እንደያዘ፤ በፕሮጀክቱ መጨረሻ ምዕራፍ አሁን ያለውን ችግር አንዴት እንደሚያሻሽል ማመላከት አለበት፡፡

**ሐ) ምን ዓይነት በጎ ተፅዕኖ ሊያመጣ ይችላል (ጥያቄ ቁጥር** 11)የሚገኘው ውጤቱ ሊሰካ የሚችል መሆኑ፤ ትግበራው በየምርቱ ላይ ምን አሴት እንደሚጨምር ማመላከት አለበት፤ ለውጡ ዘላቂነት ያለውና አንሰተኛ ባለይዞታዎችን የሚጠቅም ስለመሆኑ ያለው ብቃት

**መ) የአመልካቹ አቅም** (ጥያቄ ቁጥር ዓላማውን ለማሳካትና በተያዘለት ጊዜ ለማጠናቀቅ ድርጅቱ የቴክኒክ፤ የፋይናንስ፤ የአስተዳደር ብቃትና የሰራተኞች ልምድ አንፃር መመዘን አለበት፡፡

| መስፈርት | የመቶኛ ድርሻ (ሀ) | በገምጋሚ ከ10 የተሰጠ ነጥብ (ለ) | ውጤት ሐ= ሀ×ለ |
|---|---|---|---|
| የእሴት ሰንሰለት ፕሮጀክት ሃሳብ | 30% | | |
| የንግድ ልማት ዕቅድ | 30% | | |
| የሚያስከትለው መልካም ተፅዕኖ | 20% | | |
| የአመልካቹ የመፈጸም ብቃት | 20% | | |
| ድምር | 100% | | |

ቀን ____________________

ገምጋሚ ____________________

ፊረማ ____________________

AgroBIG

## አባሪ 3፡ የፕሮጀክት ሃሳብ ማቅረቢያ ቅጽ

**የፈጠራ፤ ሰርቶ ማሳያን ምርምር ድጋፍ ፈንድ**

(እባክዎትን ሁሉንም ጥያቄዎች የመልሱ)

---

1. **የአመልካቹ ስምና አድራሻ፡**

---

2. **ስለ አመልካቹ አጭር መግለጫ** ሀ) ህጋዊ ሰውነት ለ) የተሰማራበት የሥራ መስክ ሐ) በለፉት 3 ዓመታት ያነቀሳቀሰው የሃብት መጠን መ) የያዘው የሰራተኛ ብዛት

---

3. **ድርጅቱን ወክሎ ግንኙነት የሚያደርግ፡** ሀ) ስም ለ) በመ/ቤቱ ያለው ሃላፊነት ሐ) አድራሻ መ) ስልክ ቁጥር ሠ) ኢሜል

---

4. **የፕሮጀክቱ መጠሪያ ስም፡**

---

5. **ፕሮጀክቱ የሚገኝበት ቦታ (ወረዳ ቀበሌ)፡**

---

6. **ፕሮጀክቱ የሚተገበርበት ጊዜ፡**

---

7. **ፕሮጀክቱ ምን ዓይነት በውል የተለየ እጥረትን ለመቅረፍ እየሞከረ ነው? የተለየው ችግር ምን ያህል ከተመረጠው እሴት ሰንሰለት ጋር ይዛመዳል?**

---

8. **ፈጠራ/አዲስ አሰራር፡** የፕሮጀክቱ ውሰጥ ያለው አዲሰ ፈጠራ ምንድን ነው?

---

9. **የሚከናወኑ ተግባራት /የሥራ ወይም የምርምር ዕቅድ/፡** ፕሮጀክቱን ለመፈፀም ምን እንደሚሰራ ይገለፅ፤ ዝርዝር የሆኑ ደረጃ በደረጃ የሚተገበሩ ሥራዎች የቀመጡ፤ መቼ እንደመሰሩ ይመላከት፤ በማን እንደሚከናወን ይገለጽ

---

10. **ፕሮጀክቱን ለመተግበር ድርጅቱ ያለው ብቃት፡** **ሀ)** ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ሥራ ያለው ልምድ፤ **ለ)** ወደ ሥራ የሚያሰማራቸው ሰራተኞች የትምህርት ዝገጅት፤ **ሐ)** የፕሮጀክት ፋይናንስ አስተዳደርና ሪፖርት የማዘጋጀት ብቃት

---

11. **ከፕሮጀክቱ የሚጠበቁ ተጨማሪ ጥቅሞችና ውጤቶች፡** ከፕሮጀክቱ ትግበራ የሚገኙትን ውጤቶች የገለጹ፤ አሁን ካለው አንፃር ሲመዘን ወደፊተ የሚገኙት ጥቅሞች የገለፁ

---

12. **ታላሚ ተጠቃሚዎች፡** **ሀ)** የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች እነማን ናቸው **ለ)** ተጠቃሚዎች ስንት ናቸው /ሴት፤ ወንድ **ሐ)** ለአንሰተኛ ባለይዞታዎች የሚያስገኘው ጥቅም ምነድን ነው (ሴት/ወንድ)

13. **የበጀት ግምት፡** በሚከተሉት የወጪ ክፍሎች/ምድቦች የሚስፈልገውን የወጪ ግምት ይሙሉ
**ሀ)** የሰራተኛ ደመወዝ **ለ)** ሌሎች የዕለት ከዕለት ወጪዎች **ሐ)** የእንቨስትምነት ወጪ
**መ)** ጠቅላላ ወጪና የገንዘብ ፍላጎት ሰንጠረዥ ይያያዝ

---

14. **የፕሮጀክት ፈፃሚው አካል የመቀናጆ በጀት፡** ከፕሮጅክቱ ምን ያህሉን ወጪ በራሱ ገንዘብ ለመሸፍን ተዘጋጅቷል

---

15. **መለካት የሚችሉ የፕሮጀክት ስኬት አመላካቾች፡** ሁሉንም ሊለኩ የሚችሉ ታላሚ አመላካቾችች ይገለጹ፤ እንዴትትና መቼ እንደሚለኩ ይገለጽ

ማሳሰቢያ
የገጽ ብዛት ገደብ የለውም፡ ሀኖም ግን በተቻለ መጠን ገላጭና መረጃ ሰጪ ስፈላጊ ከሆነም አባሪዎችን ማያያዝ ይቻላል፡፡

የፕሮጀክት ሃሰቡ ለወረዳ አግሮቢግ አስተባባሪ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

## አባሪ 4፡ ፊርጂ-ብዙ ጉዳዮች መከታተያ ቅፅ

**የፈጠራ፤ ሰርቶ ማሳያን ምርምር ድጋፍ ፈንድ**

ይህ የመከታታያ ስነጠረዥ በአመልካቹ የሚሞላ ሆኖ ከፕሮጀክት ሃሳቡ ጋር መያያዝ አለበት፡፡

| | የስርዓተ-ፆታ ጉዳች | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|---|
| | በፕሮክት ዝግጅት፤ ሂደትና በፕሮጀክቱ ሃብት በመወሰን ረገድ ሴቶችና ወንዶች ተሳትፈዋል | | |
| | ከፕሮጀክቱ የሚጠበቀው ጥቅም የሴቶችንና የወንዶችን ፍላጎት፤ ቅደሚያ የሚሰጣቸውንና እጥረቶቻቸውን የሚያሟላ ነው | | |
| | የሴቶችን ችግር የሚፈቱ እርምጃዎች ተካተዋል ( ለምሳሌ በፕሮጀክት ሥራ የሚያሳልፉትን ጊዜ መጨር፣ ልጆችን የመከባከብ ሃላፊነት፤ የሴቶችን እንቅስቃሴ በመገድብ ረገድ | | |
| | የሴቶችና የወንዶች በእሴት ሰንሰለት ትግበራ ለሚወጣ ወጪና የሚገኛው ጥቅም ለየብቻው ተገምቷል (ከጊዜ አንፃር፤ ከጉልበት ዋጋ) | | |
| | **ለ. ከአካባቢ እንክብካቤ አንጻር** | | |
| | ከሮጀክቱ ጋር ተያይዞ የአካባቢ አየር ሁኔታን ሊቀይር የሚችል ሊመጣ እንደሚችል ታሳቢ ተደርጓል | | |
| | በፕሮጀክቱ ትግበራ የተሰማሩ ሰዎች ከስራው ጋር በተያያዘ የሚለቀቅ ፍሳሽ ቆሻሻ፤ንጥረ ነገር (ኬሚካል)፤ ከባድ ድመጽ፤ ጭስና መጥፎ ሽታ ለማስከተል ምክንያት ሊሆን ይችላል | | |
| | ለከፍተኛ አካባቢ ብክለትና ለጤና የማይመች ምክንያት ሊሆን የሚችልና ስጋቱን ለመቀለበስ የሚያሰቸግር ሁኔታ ይኖራል | | |
| | ፕሮጀክቱ የሚስከትለውን ችግር ለመቀነስ ወይም ለማሰወገድ የሚያስችል አማራጭ ሊኖር ይችላል | | |

## አባሪ 5፡ የፕሮጀክት ሃሳብ መገምገሚያ ቅፅ

**የፈጠራ፤ ሰርቶ ማሳያን ምርምር ድጋፍ ፈንድ**

ፕሮጀክት ማመልከቻ ቁጥር

የአመልካቹ ስም

የፕሮጀክቱ ርዕስ

ድርጅቱን ወክሎ ግንኙነት የሚያደርግ ሰው

5. የማወዳደሪያ መስፈርት (ለዝርዝሩ የማኑዋሉን ክፍል 4.5 ይመልከቱ)

| **መስፈርት** | **የተሰጠው ብደት መቶኛ (ሀ)** | **በገምጋሚው የተሰጠው ነጥብ (ከ10) (ለ)** | **ውጤት ሐ= ሀ x ለ** |
|---|---|---|---|
| ሀ. የእሴት ሰንሰለት ፕሮጀክት ሃሳብ | 15% | | |
| ለ. የንግድ ልማት ዕቅድ | 15% | | |
| ሐ. ሊያስከትለው የሚችል አወንታዊ ተጽዕኖ | 10% | | |
| መ. ትግበራ | 10% | | |
| ሠ. የአመልካቹ የመፈጸም ብቃት | 10% | | |
| ረ. ተጨማሪ ጥቅሞች | 10% | | |
| ሰ. ተጠቃሚ ታላሚዎች | 10% | | |
| ሽ. የመቀናጆ በጀት | 10% | | |
| ቀ. ውጤታማ አመላካቾች | 3% | | |
| በ. ሥረዓተ-ፆታ | 7% | | |
| በ. የአካባቢ እንክብካቤ | 5% | | |

አጠቃላይ ምልከታ

በፕሮጀክት ሃሳቡ ላይ በኢኮኖሚ፤ በማህበራዊና በቴክኒክ ጉዳይ አጠቃላይ አስተያየት መስጠት

የገምጋሚው ምክረ ሃሳብ

ማደማደሚያ

ሀ. እንዲጸድቅ ማቅረብ

ለ እንደገና እንዲከለስና ተመልሶ እንዲመጣ

ሐ. የፕሮጀክት ሃሰቡን ውድቅ ማደረግ

ቀን ______________________________

ገምጋሚው ______________________________

ፊርማ ______________________________

AgroBIG

## አባሪ 6 ሕጋዊ የበጀት ድጋፍ የውል ስምምነት

# በኢትዮ-ፊንላንድ ልማት ትብብር የአማራ አግሮቢግ ፕሮገራም

**በአግሮቢግ ፕሮገራምና**

**በ ______________________ ______________________ መካከል የተፈረመ**

**ህጋዊ የውል ሥምምነት**

የፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ በአግሮቢግ ፕሮገራም በአማራ ክልል ውስጥ በኢትዮጵያና በፊንላንድ መንግስት በተገኘ የፈይናንስ ድጋፍ የሚተገበር ነው፡፡ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የፕሮገራሙ ህጋዊ ባለቤት ነው፡፡ ቢሮው በእሴት ሰንሰለት ድጋፍ ፈንድ የሚከናወኑ ማንኛውንም ተግባር ቢሮውን በመተካት እንዲያከናውን የአግሮቢግ ፕሮገራም ድጋፍ ዩኒትን ወክሏል፤ የፕሮግራሙ ፀሃፊ ሆኖም ያገለግላል፡፡

ይህ ህጋዊ የውል ስምምነት የሁለቱን ተዋዋይ ማለትም  የአግሮ ቢግእና የ ________________

ከዚህ በኋላ የፕሮጀክት ፈፃሚ ተብሎ የሚጠራ በፕሮጀክት ትግበራ ወቅት  የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት  በዝርዝር ይዟል፡፡

1) **የፕሮጀክቱ መጠሪያ ስም፡** ይህ የውል ስምምነት የሚሸፍነው  የፕሮጀክት አስፃሚው ከፈጠራ፤ ሥረቶ ማሳያ ድጋፍ ፈንድ  የፋይናንስ ምንጭ ጥያቄ ተከትሎ ለ________________ (የፕሮጀክቱ መጠሪያ) ፕሮጀክት ማሥፈፀሚያ የሚውል ከአግሮቢግ በተገኘ ድጋፍ ለሚከናዉ ተገባራትና  በፕሮጀክቱ ሰነድ **አባሪ 1** ላይ  ለተጠቀሱና ለተፈቀዱ ወጪዎችን የሚያካትት ነው፡፡

2) **የፕሮጀክት አስፈፃሚውን ስለሚወክል ግለሰብ፡** የፕሮጀክት አስፈጻሚው ድርጅት መ/ቤቱን ወክሎ ስለፕሮጀክቱ አሰዳደርና የተለያዩ ግንኙነቶችን የሚደርግ ሰው የመድባል፡፡ የተወከለው ሰው የፕሮጀክቱን አፈፃፀም የሚያሳይ ሩብ ዓመታዊ ሪፖርት ለአግሮቢግ የማቅረብ ሃላፊነት አለበት፡፡

3) **የተፈቀደ የድጋፍ ፈንድ መጠን፡** ለዚህ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የተፈቀደው የገነዘብ መጠን በአሃዝ ብር ________________ በፊደል (________________________________________) ነው፡፡

4) **የአመልካቹ የራስ ወይም የመቀናጀ በጀት ድርሻ፡** ከላይ በተራ ቁጥር 3 የተፈቀደው በጀት ለፕሮጀክት አሰፈፃሚው ከመከፈሉ በፊት የፕሮጀክቱ የመቀናጀ በጀት ድርሻ በአሃዝ ብር ________________ በፊደል (____________________________________) ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ብቻ በተከፈተው  የባንክ ሂሳብ ቁጥር አሰቀድሞ ገቢ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

5) **ስምምንቱ ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ፡** የፕሮጀክቱ ትግበራና የተፈቃደው ገንዝብ ይህ ውል በሁለቱ ወገን ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ መጠቀም ይቻላል፡፡ ሆኖም ግነ ከተፈረመበት ቀን በፊት የወጣን ወጪን በዚህ ገንዝብ መተካት ወይም መሸፈን አይቻልም፡፡

6) **የፕሮጀክቱ የቆየታ ጊዜ፡** የፕሮጀክቱ የማጠናቀቂያ ጊዜ በፕጀክቱ ሰነድ የተገለፀውና በሁለቱ ወገን ውሉ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ _________ ወር ሆኖ ____ ቀን_____ ወር _________ ዓ/ም ይሆናል፡፡ ከውሉ ማጠናቀቂያ ቀን በኋላ የሚወጣ ማንኛውም ወጪ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ የፕሮጀክቱን የማጠናቀቂያ ጊዜ ሊራዘም የሚቸችለው ጥያቄው በጽሁፍ ለአግሮቢግ ቀርቦ ተቀባይነት አግኝቶ ሲፈቀድ ብቻ ይሆናል፡፡ የፕሮጀክቱ የማጠናቀቂያ ጊዜን ማራዘም አስፈላጊ ሲሆን የፕሮጀክት አስፈጻሚው ከሁለት ወር በፊት አስቀድሞ ጥያቄውን በፅሁፈ ለአግሮቢግ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

7) **እራሱን የቻለ የባንክ ሂሳብ ቁጥር መክፈት፡** የፕሮጀክት አስፈጻሚው ለዚህ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ብቻ የሚውል ከሌላ የፋይናንስ ምንጭ ጋር ሳይቀላቀል ራሱን የቻለ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ይከፈታል፡፡ አግሮቢግ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈለገውን ገንዘብ በዚህ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ያደርጋል፡፡ የባንክ ሂሳብ ቁጥሩ ቢያንስ በሁለት ጣምራ ፈራሚዎች የሚንሳቀስ መሆን አለበት፡፡ የፈራሚዎች የመታወቂያ ወረቀትም ፎቶ ኮፒ ተደርጎ ለአግሮቢግ መላክ አለበት፡፡ የፕሮጀክት አስፈፃሚው የተከፈተውን የባንክ ሂሳብ ቁጥር ለፕሮጀክቱ አገልገሎት ብቻ መጠቀም እንዳለበት ተስማምቷል፡፡

8) **የፕሮጀክቱ ገንዘብ አጠያየቅ፡** ለፕሮጀክቱ በየሩብ ዓመቱ የሚያስፈለገው የገንዘብ መጠን (የጥሬ ገንዘብ ፍላጎት) ከፕሮጀክቱ ሰነድ ጋር ተያይዟል፡፡ የፕሮጀክት አስፈጻሚው ከሁለት ሳምንት በፊት ከጥሬ ገንዘብ ፍላጎት በተቀመጠው መሰረት ለሩብ ዓመቱ የሚያስፈለገውን ገንዘብ አስፈላጊ ከሆኑ ደጋፊ ሰነዶች ጋር በማያያዝ አግሮቢግን መጠየቅ አለበት፡፡

9) **ገንዘብ ለመልቀቅ የሚደረግ እንቅስቃሴ፡** የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ያለበት ደረጃ ከተጣራ በኋላ የተጠየቀው ገንዘብ ይለቀቃል፡፡ የቀረበው የክፍያ ጥያቄ ተሎ ለመልቅቅ በውሉ መሠረት መሟላት ያለባቸውና በአግባቡ ተያየዘው መቅረብ ባለባቸው ደጋፊ ሰነዶች ጥራት ይወሰናል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ጉዳች ሁሉ የወረዳውን የአግሮቢግ አስተባባሪን ማነጋገር ይቻላል፡፡

10) **ገንዘብ ለመልቀቅ ቅደመ ሁኔታዎች፡** አግሮቢግ ገንዘቡን ለፕሮጀክት የሚለቀው በቅደመ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ሲሆን የፕሮጀክት አስፈጻሚው ተቀባይነት ያለው የስራ አፈጻጸም ሪፖረት፣ በፕሮጀክት ሃሰቡ በተገለፀው መሠረት መከናወን ያለበቸው ተግባራት መከናወናቸው፣ በፈንዱ ሴክረታሪያት የሚፈለጉ ተቀባይነት ያለው የሂሳብ ሪፖርትና የባንክ መግለጫዎች ተያይዘው ሲቀርቡ የተጠየቀው ገንዘብ የለቀቃል፡፡

11) **የአፈፃፀም ሪፖርት፣ ክትትልና የተገኘን ውጤት ማሳወቅ፡** የፕሮጀክት አስፈጻሚው ድርጅት እስከ ፕሮጀክቱ ማጠናቀቂያ ጊዜ ያለውን የየሩብ ዓመቱን የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለፈንዱ ሴክረታሪያት (አግሮቢግ) ለማቅረብ ተስማምቷል፡፡ የፕሮጀክቱ ትግበራን ለመከታተል ሲባል የዋጋ ሰንሰለት ድጋፍ ሂደት በውስጡ የተለያዩ ጥናቶችን ማካሄድን አፈፃፀሙን መገምገምን ሁሉ ያካትታል፡፡ ስለሆነም የፕሮጀክት አስፈፃሚው ውል ሰጪው ጥናቶችን ለማስጠናት፣ ፕሮጀክቱን ለመከታተል፣ በተለያዩ አከላላት ለሚዘጋጁ ጉብኝቶች (ልመንግስት አካል ወይም የለጋሽ ወኪል)፣ በፕሮጀክቱ የተገኙ ውጤቶችን ለማስተዋወቅ ሲባለ ለሚዘጋጁ ተግባራት ሁሉ ለመተባበር ተስማምቷል፡፡

12) **ፕሮጀከትን ማጠናቀቅ፡** በአግሮቢግ ፕሮገራም መመሪያ መሠረት የፕሮጀከት አስፈጻሚው ፕሮጀክቱ የቆይታውን ጊዜ ጨርሶ ሥራው ሲጠናቀቅ የፕሮጀክቱን የማጠናቀቂያ ሪፖርት የማዘጋጀት ሃላፊነት አለበት፡፡ የፕሮጀክቱ አስፈጻሚ የሚጠበቅበትን ሁሉ አሟልቶ ስለማጠናቀቁ የሚገልጽ የፕሮጀክት መዝጊያ ድብዳቤ ከአግሮቢግ/ከሴክረታሪያት ጽ/ቤት አስካለደረሰው ጊዜ ድረስ ፕሮጀክቱ ላይ ያሉ ስምምነቶች ሁሉ ተቀባይነት አላቸው፡፡ እነዚህ ከተፈጸሙ በኋላ ያልተከፈለው የመጨረሻ ቀሪ ገንዘብ 5% ይለቀቅለታል፡፡

13) **የፕሮጅክት ገንዘብ መወረስ፤ የካሰ ክፍያና ለማሰያዣ አለማዋል፡** የፕሮጀክት አስፈጻሚው የተለቀቀው ገንዝብ ስምምነት በተደረሰበት ተግብር ብቻ ፤ በተመደበው የወጪ ርዕስና በመጨረሻ ላይ ስምመነት በተደረገበት የፕሮጀክት እቅድ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ተስማምቷል፡፡ በተፈቀደ በጀት ላይ ከአንዱ የወጪ ርዕስ ወደ ሌላ የወጪ ርዕሰ የሚደረግ ሽግሽግ ከበጀት በላይ የወጣን ወጪ ለማስተካከል የሚደረግ ዝውውር ቅድሚያ የአግሮቢግ ስምምነት በጽሁፍ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ የፕሮጀክት አስፈሚው መ/ቤት የፕሮጀከቱን ድጋፍ ፈንድ መውረስ፤ የዕዳ ማካካሻ ማደረግ ወይም ለሦሥተኛ ወገን አሳልፎ ማስተላለፍ አይቻልም፡፡

14) **የማጭበርበር ድርጊት፡** በፕሮጀከቱ ሂደት ወቅት የፕሮጀክት አስፈጻሚው ከዚህ ውል ጋር በተያያዘ የማጭበርበር ተግባር ቢፈጽም ወይም ከላይ የተገለፁትን ማሟላት ቢሳነው፤ የፕሮጅከተ ፈፃሚው ድርጊቱን የፈጸሙትን ግለሰቦች በስም ገላፆ ማሳወቅ፤ አስፈላጊም ከሆነ በብዙሃን መገናኝ በህተመት ወይም በአየር ላይ የማወጣትና ይህም ሲደረግ አግሮቢግን ለዚህ ጉዳይ ተጠያቂ አለመሆኑን ተስማምቷል፡፡ ወንጀሉ ወይም ድርጊቱ በፕሮጀክቱ ሃብት ላይ ብክነት ወይም ምዝበራ ያስከተለ ከሆነ የአግሮቢግ ሴክረታሪያት ሃብቱን ለማስመልስና ለማስተካት ወደ ህግ ሊሄድ ይችላል፡፡ ወንጀል በፈጸሙት አካላት ላይም ክስ ይመሰርታል፡፡

15) **የፕሮጀክቱን ሂሳብና ሰነዶችን የመመለክት መብት፡** አግሮቢግ የፕሮጀከቱን ውጤትንና ማንኛውንም የፕሮጀከቱን የሂሳብ ሰነዶችና መዛግበትን በየትኛውም ጊዜ የመጎብኘትና የመመልከት መብት አለው፡፡ የፕሮጀክት አስፈፃሚው ያለምንም ገደብ ሁሉንም ሪፖርቶች፤ ሰነዶችና ከውሉ ጋር የተያያዙ ምዝገባዎችን ሁሉ ለማቅረብና ለማሳየት ተስማምቷል፡፡

16) **የፕሮጀክቱን ፈንድ ኦዲት ማድረግ፡** ይህ ስምምነት ለተደረሰበት ተግባር ማስፈፀሚያ የተሰጠው ገንዝብ የህዝብ ሀብት ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ሃበት ለታለመለት ተግባር በአግባቡ ሥራ ላይ ለመዋሉ በመንግሰት ኦዲተሮች ወይም በሌሎች በሚሰየሙ የሂሳብ መርማሪዎች ኦዲት ይደረጋል፡፡ ሁሉም የሂሳብ መዛግብትና የግዢ ሰነዶች ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ቢያነስ ለ3ዓመት ያህል ለኦዲትና ለአንዳንድ ሥራዎች አመች በሆነ መልኩ ተጠብቀው መያዝ አለባቸው፡፡

17) **ኪሳራና ጉዳት፡** የፕሮጀከት አሰፈፃሚው ስምምነት በተደረሰበት ፕሮጀክት ላይ በራሱ ድርሻ የሚጠበቅበትን ለማከነውን ሙሉ መብት አለው፡፡ ከፕሮጀክቱ ጋር በተያያዘ በህይወትም ሆነ በንብረት ላይ ለሚደርስ ጉዳት አስፈላጊውን የመድን ዋስትና ሽፋን እንዲያገኝ የማድረግ ሃላፊነት አለበት፡፡ አግሮቢግ ከፕሮጀክቱ ትግበራ ጋር ተያይዞ ለሚመጣ ማንኛውም ጉዳት ሃላፊነት የለበትም፡፡ የፕሮጀክት አስፈጻሚው በአግሮቢግም ሆነ በራሱ ሠራተኞች ላይ ጉዳት እንዳይደርስና ካላስፈላጊ ኪሰራ ለመራቅ አስፈላጊውን ጥንቃቄ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

18) **አለመግባትን ግጭትን መፍታት፡** ከፕሮጀክቱ ትግበራ ጋር በተያያዘ አለመግባባት ቢፈጠር የፕሮጀክት አስፈፃሚውና አግሮቢግ ቅራኔውን በመግባባት ለመፈታት ተስማምተዋል፤ ሆኖም ግን በሁለቱ አካላት አለመግባባቱን ለመፈታት ካልቻሉ ጉዳዩ በመንግስት በኩል ውሰኔ እንዲያገኝ ለገንዘብብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ይቀርባል፡፡

**ወር_____ ቀን_____ ዓ/ም ባህርዳር ላይ ተፈረመ**

<u>አግሮቢግ</u>

ስም

___________________________________

ሃላፊነተ

___________________________________

<u>የፕሮጀክት አስፈፃሚ</u>

ስም

___________________________________

ሃላፊነት

___________________________________

**<u>ታዛቢዎች</u>**

| **<u>ሥም</u>** | **<u>ፊርማ</u>** |
|---|---|
| 1. ______________________________ | ______________________________ |
| 2. ______________________________ | ______________________________ |
| 3. ______________________________ | ______________________________ |

***አባሪ 1***

*የተፈቀደ የፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ የፕሮጀክት ሃሳብ*

## አባሪ 7፡ የሩብ ዓመት የአፈፃፀም ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ

**የፈጠራ፣ ሥርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ**

ሪፖርቱ የሚሸፍነው ጊዜ ______________________________

የፕሮጀክቱ መለያ ቁጥርና መጠሪያ ስም ______________________________

የፕሮጀክቱ ፈጻሚ አካል______________________________

ድርጅቱን ወክሎ ግንኙነት የሚያደርግ ሰው

የሪፖርት አዘገጃጀት

**1. በተመረጡ ምርቶች የእሴት ሰንሰለት ላይ ስላለው አጠቃላይ ሁኔታ ትንታኔ**

- በዚህ ሪፖርት በተደረገበት ወቅት በተመረጡት የዋጋ ሰንሰለት ላይ በዋነኛነት የታዩ ለውጦች ምንድን ናቸው? (ለምሳሌ፡ በባለድርሻ አካላት አከባቢ፣ በገበያ፡ በዋጋ፣ በማቀነባበር)

**2. ፕሮጀክቱ ያለበት ደረጃ**

- ግብዓትን ከመጠቀም አንፃር
- በእቅድ ከተያዘው የተከናወኑ ተግባራት
- ያልተከናወኑ ተግባራት
- የተገኘ ውጤትና ያልተሳካ

**3. ውጤትን መፈተሽ /መዳሰስ/**

- የሩብ ዓመቱ ትግበራ ዋና ግብ ምን ነበር?
- ግቡ ተሳክቷል? በምን ምክንያት ተሳካ? ያልተሳካ ከሆነ ምክንያት ምን ነበር?
- ትግበራው በእቅዱ መሰረት እየሄደ ነው ወይ? ካልሆነ ምን ማስተካከያ እርምጃ ይወሰድ?
- በመጪው ሩብ ዓመት የምንጠብቀው ዋናው ውጤት ምንድን ነው?

*አባሪ 1፡ የፋይናንስ ሪፖርት*

## አባሪ 8፡ የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ

**የፈጠራ፣ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ**

ሪፖርቱ የሚሸፍነው ጊዜ ____________________

የፕሮጀክቱ መለያ ቁጥርና መጠሪያ ስም ____________________

የፕሮጀክቱ ፈጻሚ አካል____________________

| **የፕሮጀክት ክፍሎችና የወጪ ምደቦች መጠሪያ** | **የወጪ ሂሳብ መደብ** | **የባለፉት ሩብ ዓመታት ወጪ** | **የዚህሩብ ዓመት ወጪ** | **ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት** |
|---|---|---|---|---|
| 1. (የፕሮጀክት ክፍል መጠሪያ ስም) | | | | |
| 1.1 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| 1.2 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| **ንዑስ ድምር** | | | | |
| 2. (የፕሮጀክት ክፍል መጠሪያ ስም) | | | | |
| 2.1 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| 2.2 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| 2.3 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| **ንዑስ ድምር** | | | | |
| 3. (የፕሮጀክት ክፍል መጠሪያ ስም) | | | | |
| 3.1 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| 2.2 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| 2.3 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| 3.4 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| 3.5 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| **ንዑስ ድምር** | | | | |
| **ጠቅላላ ድምር** | | | | |

AgroBIG

## አባሪ 9፡ የበጀት ድጋፍ መጠየቂያ ቅፅ

**የፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ**

ቀን ___________________________________________

ሪፖርቱ የሚሸፍነው ጊዜ ___________________________________________

የፕሮጀክቱ መለያ ቁጥርና መጠሪያ ስም ___________________________________________

የፕሮጀክቱ ፈጻሚ አካል ___________________________________________

| | | |
|---|---|---|
| ለፕሮጀክቱ የተፈቀደ በጀት | ብር | |
| ባለፉት ጊዚያተ ተጠየቆ የመጣ | ሲቀነስ | |
| ከአግሮቢግ ተጠይቆ ያልመጣ | = | |

| | | |
|---|---|---|
| ከአግሮቢግ የተዛወረ ጠቅላላ የገንዘብ መጠን | ብር | |
| ሥራ ላይ የዋለ የወጪ ድምር | ሲቀነስ | |
| በድርጅቱ የሚገኝ ከወጪ ቀሪ | = | |

| | | |
|---|---|---|
| የሚቀጥለው ሩብ ዓመት የወጪ ግምት | ብር | |
| በድርጅቱ የሚገኝ ከወጪ ቀሪ | ሲቀነስ | |
| ከአግሮቢግ ለሚቀጥለው ምላክ ያለበት | = | |
| | | |
| **የማመሳከሪያ ዝርዝር** | አዎ | አይደለም |
| የባለፈው ሩብ ዓመት የፋይናንስ ሪፖርት ተያይዟል? | | |
| የሩብ ዓመቱ መጨረሻ የባንክ መግለጫ ተያይዟል? | | |
| የሩብ ዓመቱ መጨረሻ የጥሬ ገንዘብ ሚዛን ማረጋገጫ ተያይዟል? /ጥሬ ገንዘብ ቆጠራ/ | | |
| የባንክና የጥሬ ገንዘብ ሚዛን ገድርጅቱ ከወጪ ቀሪ ጋር ተመሳሳይ ነው? | | |
| የፕሮጀክቱ የሩብ ዓመት ክንውን ሪፖርት ተያይዟል? | | |
| የሚቀጥለው ሩብ ዓመት የወጪ ግምት በገልጽ ተዘጋጅቶ ተያይዟል? | | |

ፊርማ

የመ/ቤቱ ሃላፊ/ተወካይ ስም

## አባሪ 10፡ የፕሮጀክት ማጠናቀሪያ ሪፖርት ቅፅ

**የፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ**

የፕሮጀክት ትግበራ የሚሸፍነው ጊዜ ______________________________________

የፕሮጀክቱ መለያ ቁጥርና መጠሪያ ስም______________________________________

የፕሮጀክቱ ፈጻሚ አካል_______________________________________________

ድርጅቱን ወክሎ ግንኙነት የሚያደርግ ሰው ___________________________________

**የሪፖርት አዘገጃጀት**

**1. በተመረጡ ምርቶች የእሴት ሰንሰለት ላይ ስላለው አጠቃላይ ሁኔታ ትንታኔ**

- በዚህ ሪፖርት በተደረገበት ወቅት በተመረጡት የእሴት ሰንሰለት ላይ በዋነኛነት የታዩ ለውጦች ምንድን ናቸው? (ለምሳሌ፡ በባለድርሻ አካላት አከባቢ፤ በገበያ፡ በዋጋ፤ በማቀነባበር
- የፕሮጀክቱ ፈጠራ፤ የተቀመጠው መፍትሄ፤ ሠርቶ ማሳያ በእሴት ሰንሰለት ላይ ምን ያህል ተፅዕኖ አሳድሯል

**2. ፕሮጀክቱ ያለበት ደረጃ**

- ግብዓትን ከመጠቀም አንፃር
- የተሳታፊ ብዛት /ሴት/ወንድ
- በእቅድ ከተያዘው የተከናወኑ ተግባራት ፤ያልተከናወኑ ተግባራት
- የተገኘ ውጤትና ያልተሳካ ዕቅድ

**3. ውጤትን መፈተሽ /መዳሰስ/**

- የፕሮጀክቱ ግብ ምን ነበር?
- ግቡ ተሳክቷል? በምን ምክንያት ተሳከካ? ካልተሳካ ምክንያት ምን ነበር? የፕሮጀክቱ ታላሚዎች ከትገበራው መጠቀም ጀምረዋል?

**4. የፕሮጀክቱ ዘላቂነትና በሌሎች አካለት መዛመት**

- ይህ ፕሮጀክት ከተጠናቀቀ በኋላ ይቀጥላል? የሚቀጥል ከሆነ በምን የፋይናንስ ምንጭ ፕሮክቱ ወደ ሊሌች አካባቢ ተዛምቶ ይቀጥላል? በምን መልኩ ሊሳካ ይችላል?

አባሪ

የሂሳብ ሪፖርት

ስምምነት ተተደረሰባቸው የውጤተ አመላካቾችና የሚመዘኑ ውጤቶች

AgroBIG

## አባሪ 11፡ የቡድን ተኮር ማወያያ ቅፅ

**የፈጠራ፤ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ**

ከፕሮጀክቱ ትግበራ መጨረሻ ላይ ከተወሰኑና ከሚመለከታቸው ቁልፍ ባለድርሻ አካለት ጋር ቡድን ተኮር ስበሰባ የሚደረግ ሲሆን ዓላማውም ስለፕሮጀክቱ ውጤት ለመወያየትና ለመግምገም ነው፡፡ የዚህ ዓይነት ውይይት የባለድረሻ ካላትን ልምድ ለማወቅ መልካም አጋጣሚ ነው፡፡ ለቡድን ተኮር ውይይት የሚጠሩ ተሳታፊዎች በተቻለ መጠን የሴቶች ተሳትፎ ተመጣጣኝ መሆኑንና ሁሉም አባላት ሃሳባቸውን ያለችግር እንዲገልፁ የሚያበረታታ መሆን አለበት፡፡

**የቡድን ተኮር ውይይቱ በ3 ጉዳች ላይ ያተኩራል፡፡**

**1. ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች**

- የፕሮጀክቱ ዓላማ ምን ነበር? ፕሮጀክቱ ዓለማውን አሳክቷል ወይስ አላሳካም? ለውጤታማነቱ ወይም ላለመሳካቱ ምክንያቶች ምን ነበሩ?
- የፕሮጀክቱ አዲስ ፈጠራ ገፅታ ምን ነበር? እንደታሰበው ሥራ ላይ ውሏል? ለታላሚዎች /ሴቶችና ወዶች/ ከፕሮጀክቱ ምን ጥቅም አገኙ?
- የቡድን ተኮር ተወያዮች በፕሮጀክቱ ምክንያት በኑሯቸው ላይ መሰረታዊ የሆነ የገቢ መጨመር፤ የምርት ማደግ፤ የተሸለ የመሸጫ ዋጋ ማገኘት፤ ሌሎች ተጨባጭ መፍተሄዎች ተመለክተዋል?

**2. ለፕሮጀክቱ ታላሚዎች በተጨባጭ የታየ ለውጥ**

- የአግሮቢግ ወረዳ አስተባባሪ በውይይቱ ወቅት ከተሳታፊዎች ምን መሰረታዊና ተጨባጭ ለውጥ እንዳገኙ መለየት ይኖርበታል፡፡
- ከውይይታቸው በፊት የተወሰኑ ተሳታፊዎች ቃለምልልስ (በአባሪ 12 መሠረት) ያደርጋሉ፡፡ የአግሮቢግ ወረዳ አስተባባሪ የተደረገው ቃለምልልስ የሁሉንም አርሶ አደሮች ሃሳብ የሚወክል ስለመሆኑ አወያይቶ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ ለምሳሌ የታየው የምርት መጨመር ለተወሰኑ የቡድን አባላት ወይስ ለሁሉም ስለመሆኑ (ሴት/ወንድ ለያይቶ ማየት ይቻላል)፡፡

**3. ፈርጀ-ብዙ ጉዳዮች ላይ መወያየት**

የፈጠራ፤ ሠርቶማሳያና ምርምር ድጋፍ ፕሮጀክቶች መነሻቸው የተለያየ ቢሆነም በሁሉም ላይ የፈርጀ-ብዙጉዳች በውል መመልከት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የሚደረገው ውይይት ፈርጀ-ብዙ ጉዳዮች መከታተያ ቅጽ አባሪ 4 መሰረት አድረጎ ይሆናል፡፡ የወረዳው አግሮቢግ አሰተባባሪ እንደ አመቻችነቱ በቡድኑ ውይይት ወቅት የተደረሰባቸውን የማደማደሚያ ሃሳቦች ሪፖርት ማደረጉ አስፈላጊ ነው፡፡ የተሞላው የመከታተያ ቅጽ ለፈንዱ ሴክረታሪያት ከሚላከው ሪፖርት ጋር እና በአንዳንድ በጣም ጠቃሚ በሆኑ ግኝቶች ላይ ከነማብራሪው ተያይዞ ይለካል፡፡

አባሪ 12፡ የተጠቃሚዎችን ምስክርነት ማሰባሰብያ ቅፅ

**የፈጠራ፣ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ**

አንድ የፕሮጀክት ተጠቃሚ አርሶአደር በሕይወቱ ያገኘውን ለውጥ ለሌላው የምስክረነት ቃሉን

የሚሰጥበት ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት መረጃዎችን መሰብሰብ አርሶአደሮች ሃሳባቸውን በግለጽ ለመግለፅ የረዳቸዋል፡፡ ዋናው ቁም ነገርና መተኮር ያለበት ጉዳይ ከፕሮጀክቱ ጋር ተያይዞ ምን ተግባር እንደተከናወነ፣ ምን ውጤት እንዳገኘ ያለውን ስሜት ማወቅ ነው፡፡

ይህም የፕሮጀክቱን አፈጻፀም አሳታፊ በሆነ መልኩ ለመገምገምና ትምህርት ለመውሰድ ያግዛል፡፡ የዚህ ዓይነት መረጃ የተገኘውን ውጤት አጋኖ እንዳይነገር ከማደረጉም በላይ ከባለቤቱ በቀጥታ ትክክለኛውን መረጃ የሚገኝበት ዘዴ ነው፡፡ የታሪኩ ጸሃፊ አርሶ አደሩ በሕይወቱ ላይ ምን ጥሩ ለውጥ እንደመጣ፣ ወይም ያልጠቀመው እንደሆነ፣ ወይም ምንም ለውጥ እንዳልመጣ ከገለፀ ለምን እነዚህ ክስተቶች እንዳጋጠሙት ምክንያቱን አካቶ መፃፍ አለበት፡፡

**የወረዳው አስተባባሪ በፈጠራ፣ ሠርቶ ማሳያና ምርምር ድጋፍ ፈንድ** በአንድ ፕሮጀክት ላይ ቢያንስ 2 ታሪክ አንድ ሴትና ሌላ አንድ ወንድ መጻፍ አለበት፡፡

ዓላማውም ከዚህ በታች የተመለከቱትን መረጃዎች ለማሰባሰብ ነው

ሀ. ከፕሮጀክቱ ትግበራ በፊት የነበረውን ሁኔታ ምን የመስል ነብር? (መነሻ መረጃ)

ለ. በትግበራ ወቅት ምን ተፈጠረ/ተደረገ? (የተከናወኑ ተግባራትን የተገኙ ውጤቶች)

ሐ. ከትግበራ በኂላ በተጠቃሚዎች ላይ ምን መሰረታዊ የሆነ ለውጥ መጣ? ( የፕሮጀክቱ አስተዋጽዖ ምንድን ነው?)

**ትረካውን ለመፃፍ ሦስት ደረጃዎች አሉት**

1. መሰረታዊ መረጃዎችን መሰብሰብ
2. ቃለ-መጠይቅ ማድረግና ፎቶግራፍ መውሰድ
3. ትረካውን መፃፍ

**ሂደት 1. መሰረታዊ መረጃዎችን መሰብሰብ**

1. የገበሬው ስም፣ ዕድሜ፣ ፆታ፣ የቤተሰብ ሁኔታ፣ የልጅ ብዛት
2. የሚወክለው የህበረተሰብ ክፍል (መሪ፣ ተመሪ፣ ድሃ፣ መካከለኛ፣)

3. የሚያመርተው ምርት ገበያ ተኮር ወይስ የመግበ ሰብል (የት አካባቢ)

4. ሌሎች የማምረቻ የሃብት /መሳሪያዎች (በክበት ፤ የውሃ ማሳቢያ ሞተር)

5. በፕሮጀክቱ ስንት ገበሬዎች ተሳታፊ ነበሩ

6. ከፕሮጀክቱ ምን ያህል አርሶ አደሮች ተመሳሳይ ልምድን ውጤት አኝተዋል

**ሂደት 2. የቃለ-መጠይቅ አጠቃላይ ይዘት**

7. ፕሮጀክቱ ምን ለማከናወን ነበር የሞከረው

8. ገበሬዎች በፕሮጀክቱ ትግበራ ላይ እንዴትና ለምን ተሳተፉ

9. ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ ከ1 ዓመት በፊት አርሶ አደሩ ሕይወት ምን የመስል ነበር

10. በአሁኑ ስዓት ምን የተለየ ነገር አለ? ለአርሶ አደሮች የተለያዩ አገልግሎቶችን በማቅረብ፤ በሰብል ምርትና በግብይት፤ በተለያዩ የገበሬዎች አደረጃጀት

11 በፕሮጀክቱ ምክንያት ለተጠቃሚዎች የመጣው ትልቅ ለውጥ ምንድን ነው?

12. የገበሬዎች ገቢያቸው አድጓል? የገኙትን ገንዘብ እንዴት እየተተቀሙበት ነው?

13. ፎቶገራፋቸውን ለመውሰድ ፈቃድ መጠየቅ ከተቻለም ከግብርና ስራቸው ጋር የተያያዘ ፎቶግራፍ ወይም ካፈሩት ቋሚ ንብረት ጋር ቢሆን ይመረጣል።

**ሂደት 3 ታሪኩን መፃፍ**

- ከታሪኩ ጋር የሚስማማ አጭርና ገላጭ ርዕስ መሰጠት
- ቃለ-ምልልስ ባደረገው /ችው ግለስብ መሰረታዊ መረጃ መጀመር
- ትረካው በተቻለ መጠን
    - ሀ. ከፕሮጀክት ትግበራ በፊት የነበረውን (መነሻ መረጃ)
    - ለ. በፕሮጀክቱ የተከናወኑና የተገቶኙ ውጤቶች
    - ሐ. በገበሬው ሕይወት ላይ የፈጠረው ልዩነት
- ታሪኩ በአማርኛ ወይም በእግሊዘኛ እስከ 3 ገጽ ሊሆን ይችላል። ትረካው በአማርኛ ከሆነ የፈነዱ ሴክረታሪያት ለመረጃ ሲባል ወደ እንግግሊዘኛ ይመለሳል
- ከፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ሪፖረት ጋር ቢያነስ 2 ትረካዎችን / ፎቶገራፎችን/ በማያያዝ በኢሜል ለፈንዱ ሴክረታሪያት መላክ ይኖርበታል።